ትምህርት አሥራ ሦስት

ኢሳይያስ 40–42

የመጀመሪያ ቀን ኢሳይያስ 40

ወደ ሩቅ አገር ሄደህ የአንተን ባሕል በማያውቅ ሀብታም ሰው ቤት በባርነት ታገለግላለህ እንበል። ሰውዬው ስለማያምንህ በሆነው ባልሆነው ይደበድብሃል። ሃይማኖትህ ለዚህ ሰው እንግዳ በመሆኑ የአባቶችህን አምላክ እንዳታመልክ ያግድሃል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር በዚህ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ ብትጸልይም ምላሹ ሳይመጣ ዓመታት ተቆጠሩ። ዕድሜህ እየገፋ ሄዶ በማርጀትህ ከሞት ደጃፍ ላይ እንደቆምህ ተሰማህ። ልጆችህና የልጅ ልጆችህም በባርነት ቀንበር ሥር ይማቅቃሉ። ተስፋ የምታደርገው ነገር ቢኖር ከአንድ መቶ ሃምሳ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር አንድ ቀን ሕዝብህን ከዚህ አስከፊ ጭቆና ነፃ እንደሚያወጣ የተነገረው ትንቢት ብቻ ይሆናል።

1ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብትገኝ ስሜትህ ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚችል ግለጽ። ለ) በእነዚህ አስቸጋሪ ቀናት በእግዚአብሔር ላይ ያለህን ተስፋ ለማጽናት የምታደርጋቸው አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው? ሐ) እምነታቸውንና ተስፋቸውን ያጠናከርላቸው ዘንድ ለልጆችህና ለልጅ ልጆችህ ምን ምክር ትሰጣቸዋለህ? መ) ዛሬ ክርስቲያኖች የሚጋፈጧቸው አንዳንድ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው? ሠ) በትንቢተ ኢሳይያስ ጥናታችን መሠረት፥ ለዚህ ሰው ምን ምክር ትሰጠዋለህ?

በታሪክ ሁሉ ሕዝበ እግዚአብሔር በተለያዩ ችግሮች ውስጥ አልፈዋል። ብዙዎች ለባርነትና አለፍላጎታቸው ወደ ጦርነት ለመዝመት ተገድደዋል። አንዳንዶች የሚጠጉባቸው ቤተሰቦች ሳይኖሩ ለመበለትነትና ለእጓለማውታ ተዳርገዋል። አንዳንዶቹም ተርበዋል። እንደ እነዚህ ባሉት ጊዜያት የእግዚአብሔር ሕዝብ በእምነቱ መጽናቱ ወሳኝ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ ጨለማ መካከል በእምነት ለመጽናት ደግሞ የእግዚአብሔርን ባሕርያትና ለልጆቹ የገባቸውን የተስፋ ቃሎች ማወቁ አስፈላጊ ነው። ስለ እግዚአብሔርና ስለ ኃይሉ ያለን መረዳት ሲደበዝዝ፥ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች ከመጠበቅ ወደ ኋላ እናፈገፍጋለን። ከዚያ በኋላ በእግዚአብሔር ላይ ያለንን እምነት ክደን እንደማያምኑት ሰዎች ለመሆን ጊዜ አይፈጅብንም።

ኢሳይያስ ወደፊት ስለሚመጣው የከበረ የመሢሑ መንግሥት ቢናገርም፥ ብዙዎቹ ከኢሳይያስ 1–35 የሚገኙ ትንቢቶች በይሁዳ ሕዝብ ላይ በቅርቡ በሚመጣው ፍርድ ላይ የሚያተኩሩ ነበሩ። ያም ፍርድ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለሌሎች አገሮች በባርነት እንዲሸጡና በአሕዛብ አገሮች ሁሉ እንዲበተኑ የሚያደርግ ነበር። አይሁዶች እነርሱን ወይም ሃይማኖታቸውን በማያውቁ ሰዎች ይንገላታሉ። እግዚአብሔር

በምርኮኛነት የሚወሰዱ ሕዝቦች ታማኞች ሆነው ይቆዩት ዘንድ ወደፊት የሚያገኛቸውን በረከትና የመሢሑን ምጽአት ሲጠባበቁ ሊያጸናቸው የሚችለውን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ይገልጽላቸዋል። ስለሆነም ከኢሳይያስ 40–66 ባሉት ክፍሎች እግዚአብሔር በርካታ አበረታች የተስፋ ቃሎችን ይሰጣል። ከእነዚህ የተስፋ ቃሎች መካከል አንዳንዶቹ አይሁዶች ከሰባ ዓመታት ምርኮ በኋላ ወደ አገራቸው በሚመለሱበት ወቅት በቅርቡ የሚፈጸሙ ነበሩ። ብዙዎቹ ግን አይሁዶችና ክርስቲያኖች የመሢሑንና ሊነግሥ የሚመለሰውን የኢየሱስ ክርስቶስን ምጽአት በሚጠብቁበት ጊዜ ተስፋ ይሆኗቸው ዘንድ ሳይፈጸሙ ቆይተዋል።

በኢሳይያስ 40–66 ይሁዳ በባቢሎን ከመማረኳ ከአንድ መቶ ዓመታት በፊት ትንቢት ተነግሮአል። አጻጻፉ ግን ከስተቶቹ ተፈጽመው ካለፉ በኋላ እንደተጻፈ ዓይነት ነው። እግዚአብሔር ስለተናገረ የሚፈጸም መሆኑ ኢሳይያስን አላጠራጠረውም። አይሁዶች የእግዚአብሔርን ባሕርያት አጥርተው ማወቃቸው ወሳኝ እንደሆነ ነቢዩ ተገንዝቦአል። እግዚአብሔር ከጣዖታትና ከአሕዛብ የአምልኮ ሥርዓቶች የተለየ መሆኑን ማወቅ ነበረባቸው። እንዲሁም ደግሞ አገሮች የኋላ ኋላ በእግዚአብሔር እንደሚረቱ ማወቅ ያስፈልጋቸው ነበር። ይህም በአሕዛብ መካከል ሲኖሩ ለእግዚአብሔር ታማኝ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል። ስለሆነም በቀሪዎቹ ገጾች ኢሳይያስ ለሕዝቡ የማጽናኛ መልእክቶችን ጽፎአል። በነዚህ ምዕራፎች ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት እጅግ አስደናቂ ትንቢቶች አንዳንዶችን እንመለከታለን። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ለመግዛት ስለሚመጣበት ስለ መጨረሻው ምጽአት ብቻ ሳይሆን ለሰዎች ኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ ስለሚሞትበት ስለ መጀመሪያው መምጣቱ ጭምር ነው።

ምዕራፍ 40–48 ከትንቢተ ኢሳይያስ የመጨረሻ ክፍል የመጀመሪያው ነው። ክፍሉ በሦስት የእግዚአብሔር ባሪያዎች ላይ ያተኩራል። ስለ እነዚህ ሦስት ባሪያዎች የሚነገሩት ትንቢቶች የእግዚአብሔር ሕዝቦች እርሱ ነፃ እስኪያወጣቸው ድረስ በእግዚአብሔር ታምነው ተስፋ እንዲያደርጉ ያበረታታሉ። አይሁዶች እምነትና ተስፋ ለማግኘት ወደ ጣዖታት እንዳይመለሱ መጠንቀቅ ይኖርባቸው ነበር። የዚህ ክፍል ትምህርቶች በሁለት ዐበይት የሥነ-መለኮት እውነቶች ላይ የተንተራሱ ናቸው።

1. እግዚአብሔር ፍጥረቱን ሁሉ በመቆጣጠር ላይ የሚገኝና ከመረጣቸው ጋር የፍቅር ግንኙነቱን የሚጠብቅ አምላክ ነው።

2. እግዚአብሔር የታሪክ ገዥ በመሆኑ በምድር ላይና በሰዎች ሕይወት የሚፈጸመውን ነገር ሁሉ ይቆጣጠራል።

2ኛ ጥያቄ፡– ኢሳይያስ ምዕራፍ 40ን አንብብ። (ሀ) በቁጥር አንድ ለኢሳይያስ የተሰጠው ትእዛዝ ምንድን ነው? የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚጽናናው ለምንድን ነው? (ለ) በቁጥር 3 የተሰጠው ትእዛዝ ምንድን ነው? ማቴ. 3፡3፤ ዮሐ. 1፡23 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች የኢሳይያስን ትንቢቶች ማን እንደፈጸማቸው ይናገራሉ? እንዴት ፈጸማቸው? (ሐ) የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የተነጻጸረው እንዴት ነው? ኢሳይያስ ሁለቱን የሚያነጻጽራቸው ለምን ይመስልሃል? (መ) በኢየሩሳሌም የሚነገረው መልካም የምሥራች ምንድን ነው? አንተ በምርኮኝነት ተወስደህ ቢሆን ኖሮ ይህ ክፍል (ኢሳ. 40፡9–11) እንዴት ያበረታታህ ነበር? (ሠ) በኢሳይያስ 40፡12–26 የተገለጹትን የእግዚአብሔርን ባሕርያት ዘርዝር። እግዚአብሔር ከጣዖታት፥ ከአገሮችና ከመሪዎች፥ ወዘተ... ጋር የተነጻጸረው እንዴት ነው? እግዚአብሔር በምርኮ ለሚገኙት አይሁዶች ይህንን ገለጻ የሰጠው ለምንድን ነው? (ረ) ያዕቆብ በእግዚአብሔር ላይ ያጉረመረመው ምን በማለት ነበር? አንተ ወይም አንተ የምታውቀው ሌላ ሰው እግዚአብሔርን በተመሳሳይ ሁኔታ የከሰሰው እንዴት ነው? (ሰ) እግዚአብሔር ለዚያ ክስ የሰጠው ምላሽ ምንድን ነው? ስለ ራሱ ምን ይነግረናል? በመከራ ጊዜ ከሕዝቡ ጋር ስላለው ግንኙነት ምን ይላል? (ሸ) የዚህን ምዕራፍ ዐበይት ትምህርቶች በአንድ አንቀጽ አጠቃልለህ ጻፍ።

1. ይሁዳ የምትጽናናበት የመጀመሪያው ምክንያት፥ የቅጣቷ ወራት መፈጸም (ኢሳ. 40፡1–2)

ትንቢተ ኢሳይያስ የሚጀምረው የእግዚአብሔር ዓመፀኛ ልጅ የሆነችውን ይሁዳን በመግለጽ ነው (ኢሳ. 1)። ይህ በእግዚአብሔር ላይ የተፈጸመው ዓመፅ ወደ እግዚአብሔር ፍርድ መርቶአቸዋል። ይኸውም መጀመሪያ በአሦራውያን፥ የኋላ ኋላ ግን ወደ ምርኮ በወሰዱአቸው ባቢሎናውያን እጅ እንዲወድቁ አድርጎአቸዋል። እግዚአብሔር ልጆቹ ለሰባ ዓመታት እንደሚቀጡ ተናግሮአል (ኤር. 25፡8–12 አንብብ)።

ምንም እንኳ ኢሳይያስ የጻፈው ከምርኮው አንድ መቶ ዓመታት በፊትና ከአይሁዳውያን መመለስ አንድ መቶ ሰባ ዓመታት ቀደም ብሎ ቢሆንም፥ በዚህ ክፍል መልእክቱን የገለጸው የሚለቀቁበት ዘመን እንደመጣ አስመስሎ ነው። ስለሆነም ሁለተኛውን ዐቢይ ክፍል (ምዕራፍ 40–66) «ተጽናኑ» በሚል ቃል ጀምሮአል። እግዚአብሔር ነቢዩ ቃሉን በመስጠት ሕዝቡን እንዲያጽናናቸው ይሻል። በዕብራይስጥ ቋንቋ አንድን ቃል ደግሞ መጻፍ የማጋነን ምልክት ስለሆነ፥ ኢሳይያስ «አጽናኑ፥ ሕዝቤን አጽናኑ» በማለት ሁለት ጊዜ ገልጾአል። ይህም «በሚገባ አጽናኑ» እንደ ማለት ነው። አባት ጉዳት ለደረሰበት ልጁ በፍቅር እንደሚናገር ሁሉ፥ እግዚአብሔርም ሰባ ዓመታት በምርኮ

ለተሠቃየው ልጁ ለይሁዳ በፍቅር ተናገረ። እግዚአብሔር የተመረጠው ሕዝቡ የሚጽናናባቸውን አያሌ ምክንያቶች ያቀርባል።

ሀ. «*የተቀጠረችበት ወራት እንደ ተፈጸመ*»። «የተቀጠረችበት ወራት» የሚለው ሐረግ ለአንድ ዓላማ ማከናወኛ የሚያገለግለውን ረዥም ና አስቸጋሪ ጊዜ የሚያመለክት ነው። በእግዚአብሔር ላይ ለፈጸሙት ዓመፅ ቅጣት ይሆናቸው ዘንድ እግዚአብሔር አይሁዶችን ወደ ባቢሎን ልኮአቸዋል። የአይሁዶች ምርኮ ቀደም ሲል ወደነበረው የግብፅ ባርነት እንደመመለስ ተደርጎ ተገልጾአል። ባርነት በምንም መልኩ ቀላል አይደለም። የጌቶቻቸውን አግባብነት የጎደለው አያያዝና ለሴሎች ጥቅም ሲባል ከባድ ተግባር ማከናወንን ያካትት ነበር። በዚህ ወቅት መራራ ጊዜ አብቅቶ እግዚአብሔር ሊያድናቸው እየቀረበ ነበር።

ለ. «*ኃጢአትዋም እንደ ተሰረየ*»። በዚህ ስፍራ የቀረበው አገላለጽ የሚያሳየው ብድር ውስጥ በመዘፈቁ ምክንያት እንደ ባሪያ መሸጥ ስለነበረበት ሰው ነው። ያ ሰው ነፃ ከመውጣቱ በፊት ለተወሰነ ጊዜ በመሥራት ክፍያውን ማጠናቀቅ ነበረበት (ለምሳሌ ዘሌ. 26፡41)። በተመሳሳይ ሁኔታ በፍርድ እግዚአብሔር ይሁዳን ለባቢሎን ባርነት ሽጦአታል። አሁን ግን በእግዚአብሔር ላይ ለፈጸመችው ዓመፅ የተሰጣትን ቅጣት ጨርሳለች። በምርኮኛነቷ ዕዳዋን ለእግዚአብሔር ስለከፈለች የቅጣቱ ጊዜ አብቅቶአል። (ማስታወሻ፡ ይህ ስለ ግላዊ ደኅንነት የሚናገር አይደለም። የኃጢአት ዕዳችንን በራሳችን ተግባር ልንከፍል አንችልም። ይቅርታ ሁልጊዜም ነፃ ስጦታ ነው። ይህ ጥቅስ የሚናገረው ስለ ብሔራዊ ቅጣት ነው። በቅጣት እግዚአብሔር ለይሁዳ የሰባ ዓመታት ምርኮ ወስኖአል። አሁን የባቢሎን የሰባ ዓመታት ባርነት ስላበቃ እግዚአብሔር ይሁዳን ነፃ ያወጣታል።)

ኢሳይያስ የይሁዳን ቅጣት ክብደት «ስለ ኃጢአትዋ ሁሉ ሁለት እጥፍ እንደተቀበለች» ሲል ይገልጻል። በዕብራይስጥ ቋንቋ «እጥፍ» የሚለው ቃል በእግዚአብሔር የተወሰነው ፍርድ መጠናቀቁን ያመለክታል። እንዲሁም ደግሞ ቅጣቱ ከበደሉ ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ያመለክታል። ስለሆነም እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ይሁዳ ለዓመፅ ተግባርዋ ሙሉ ለሙሉ እንደከፈለችና ከቅጣትና ከምርኮ የምትላቀቅበት ጊዜ እንደደረሰ ገልጾአል። ይህ አንድ እስረኛ የተወሰነበትን የአሥር ዓመት ቅጣት በእስር ቤት ውስጥ ፈጽሞ ነፃ እንደሚለቀቅ ማለት ነው።

አንዳንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ስናምጽ ይቅርታው ኃጢአታችን የሳበውን መዘዝ እንዳንጋፈጥ ይታደገናል። ነገር ግን እኛ ከስሕተታችን እንማር ዘንድ እግዚአብሔር የኃጢአት ተግባራችንን ዋጋ እንድንከፍል የሚያስገድድበት ዘመን አለ። ይቅርታ ማለት እግዚአብሔር ሳይቀጣ

ይተዋል ማለት አይደለም። ለዚህም ለኃጢአታቸው የእግዚአብሔርን ይቅርታ የጠየቁት ጻድቃን አይሁዶች ከምርኮው ነፃ አለመሆናቸውን መረዳቱ ጠቃሚ ነው። እግዚአብሔር ነፃ ከማውጣቱ በፊት የቅጣትና የምርኮ ጊዜ መጠናቀቅ ነበረበት። ከጋብቻ ውጭ ያመነዘረች ሴት ንስሐ በምትገባበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታን ታገኛለች። ነገር ግን እግዚአብሔር በአእምሮዋ ውስጥ እንደ ካስማ ተሰንቅሮ የሚቀረውን ጸጸት ወይም በዝሙቱ ሳቢያ ተፀንሶ በደሏን ሊያስታውሳት የሚኖረውን ልጅ አይከላከልላትም። ኃጢአት አንዳንድ ጊዜ ከአእምሮ ውስጥ የሚቀር መራራ ፍሬ አለው። እንደ ባርነትም ይዞ ለመቆየት ይከብዳል። እግዚአብሔር ግን ያንን ባርነት እንደሚያስወግደው ማረጋገጫ ይሰጠናል። ወዲያው ይቅርታ ይደረጋል። የአእምሮ ጸጸታችንንና የስሕተታችንን መዘዞች ሳይቀር እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ለዕድገታችን ልንማር ወደምንችልበት አቅጣጫ ይለውጠዋል። በተመሳሳይ መንገድ የአይሁዶችን ምርኮ የውሸት አማልክትን ለማገልገል ያላቸውን ፈተና ለመቅረፍ ይጠቀምበታል። ነገር ግን አገራቸው በዳዊትና በሰሎሞን ዘመን እንደነበረው ክብርና ነጻነት ልትቀጥል አትችልም ነበር።

3ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ ልንጠይቅ እንደምንችልና ዋጋ መክፈል እንደማያስፈልገን በማሰብ ኃጢአትን አቅልሎ ስለመመልከት ከዚህ ምን እንማራለን? ለ) ይህ ብዙዎች ስለ ይቅርታ ከሚያስቡት የሚለየው እንዴት ነው?

2. ይሁዳ የምትጽናናበት ሁለተኛው ምክንያት፣ የሚመጣውን የእግዚአብሔር ማዳን የሚያውጁ ሦስት ድምፆች (ኢሳይያስ 40፡3–11)

ሀ. የመጀመሪያው ድምጽ፣ እግዚአብሔር ክብሩን ለሰው ልጅ ይገልጣል (ኢሳ. 40፡3–5)

ኢሳይያስ እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማጽናናት የሚያመጣውን ነፃ የማውጣት ተግባር የተለያዩ ገጽታዎች የሚያውጁትን ሦስት ድምፆች ገልጾአል (ኢሳ. 40፡3፥ 6፥ 9 ተመልከት)። የመጀመሪያው ድምፅ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንደሚጎበኝና ክብሩን እንደሚገልጥላቸው ገልጾአል። በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ክብር እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር መኖሩን (ዘጸ. 16፡10)፥ በተአምራት የሚታዩትን የእግዚአብሔር የኃይል ተግባራት (ዘጸ. 16፡7)፥ ወይም የእግዚአብሔርን ባሕርይ መገለጥ [መዝ. (79)፡9] ያመለክታል። ይህ የማን ድምፅ እንደሆነ ባይነገረንም፥ እንደ እግዚአብሔር መልእክተኛ የሚናገር የሰው ድምፅ ይመስላል። ዋናው የተናጋሪው ማንነት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀብሎ የሚናገረው መልእክት ነው።

ኢሳይያስ እግዚአብሔር ዓለምን ለመባረክ ሲመጣ ዓለም የምትዘጋጅበትን ሁኔታ ለመግለጽ ጥንታዊ ባሕል ተጠቅሞአል። አንድ ንጉሥ ከተማን ከመጎብኘቱ በፊት ሕዝቡ ወጥተው ጎዳናውን ያስተካክሉለታል። ይህም ንጉሡ በአባጣ ጎርባጣ መንገድ እንዳይቸገር ለማድረግ የሚካሄድ ተግባር ነበር። (በኢትዮጵያም ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንድን አካባቢ ከመጎብኘታቸው በፊት ብዙ የመንገድ ጥገናዎች ይካሄዳሉ።) እግዚአብሔር ሕዝቡን ከመጎብኘቱ በፊት ይሽው ተመሳሳይ ነገር ይፈጸማል። ሕዝቡም ንጉሣቸው እግዚአብሔር ሰርጓጉጥ በሌለበት ጎዳና ይመላለስ ዘንድ ራሳቸውን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ይህ ማለት በሕይወታቸው ውስጥ የሚገኝ ማንኛውንም ኃጢአት መናዘዝ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔርም ደግሞ መንገዱን ለማዘጋጀት አብርአቸው ይሠራል። የመንግሥታትን ልብ በማዘጋጀት አይሁዶች ወደ አገራቸው ይሄዱ ዘንድ እንዲለቁዋቸው ያደርጋል። እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዲጎበኝና ወደ አገራቸው መመለስ እንዲችል በእግዚአብሔር ሕዝቦች ልብም ሆነ በዓለም ሁኔታዎች ነገሮች መዘጋጀት አለባቸው።

በዚህ ዓውድ፥ የእግዚአብሔር ጉብኝት ሕዝቡ ወደ አገራቸው በሚመለሱበት ጊዜ ለሰዎች ሁሉ የሚገለጸው የእግዚአብሔር ክብር ይመስላል። በዘጸአት መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ግብፃውያን አይሁዶችን ይለቁዋቸው ዘንድ በፈርዖን በኩል እንደተጠቀመ ሁሉ፥ አሁንም የአሕዛብን መንግሥታት በመጠቀም ሕዝቡ ከምርኮአቸው ተላቅቀው ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ያደርጋል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ወደ አገራቸው ለመመለስ ሲሠራ ለሰዎች ሁሉ ኃይሉንና ክብሩን ያሳያል (ኢሳ. 35፡2፤ 44፡23፤ 52፡10)። ስለሆነም ቀዳሚው ትንቢት የሚናገረው ስለ አይሁዶች ከምርኮአቸው መለቀቅ ነው። ዳሩ ግን ይህ ትንቢት አንድምታ ስለነበረው ስለ ሌላም ዝግጅት አገልግሎአል።

በአዲስ ኪዳን መጥምቁ ዮሐንስ ይህንን ትንቢት እንደፈጸመው ተጠቅሶአል (ማቴ. 3፡3)። እግዚአብሔር ለእርሱ የሰጠው አገልግሎት ለአይሁድ ንጉሥ ማለትም ለመሢሑ መንገድ ማዘጋጀት ነበር። ዐቢይ አገልግሎቱ የተፈጸመው የእግዚአብሔር ነቢይ ሆኖ ባገለገለበት ምድረ በዳ ነበር። መልእክቱም «የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» የሚል ነበር (ማቴ. 3፡1)። ብዙ ሰዎች መልእክቱን ሰምተው ንስሐ በመግባት ተጠምቀዋል። በዚህ ዓይነት ለመሢሑ መምጣት ራሳቸውን አዘጋጅተዋል። መጥምቁ ዮሐንስ እግዚአብሔርን የሚቃወሙትን ልቦች ዝቅ በማድረጉና የሕዝቡን ልብ በማዘጋጀቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ብዙዎች በእርሱ አምነዋል። ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ በታሪክ ማንም አድርጎት በማያውቀው መንገድ

የእግዚአብሔርን ክብር ገልጦአል። ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔን ያየ አብን አይቶአል» ብሎአል (ዮሐ. 1፡14፤ 11፡4፥ 40፤ 17፡4–5፤ ዕብ. 1፡3)።

የዚህ ትንቢት ሦስተኛ አፈጻጸምም ሊኖር ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ወደ ምድር ከመመለሱ በፊት ለነገሥታቱ ንጉሥ ምጽአት ምድርን የሚያዘጋጁ ሁለት ምስክሮች እንደሚነሡ ከራእይ 11፡1–13 እንረዳለን። በተጨማሪም እግዚአብሔር መሢሑ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ለመግዛት ከሰማይ በሚወርድበት ጊዜ የሕዝቡን ልብ ለማዘጋጀት የተለያዩ ፍርዶችን ይጠቀማል። በዚያን ጊዜ ዓይኖች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ የምድር ንጉሥ እንደሆነ አይተው ይለያሉ። የእርሱን ንግሥና የሚቃወሙትን በፍርድ በማስወገድ በእርሱ ያመኑትንና በታማኝነት የተከተሉትን ይሸልማቸዋል። ከዚያም በኋላ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የእግዚአብሔር ክብር ለሰዎች ሁሉ ይገለጻል (ማቴ. 16፡27፤ 24፡30፤ 25፡31፤ ራእ 1፡7)።

ለ. ሁለተኛው ድምፅ፡ ምንም እንኳ የሰው ልጅ ጊዜያዊ ቢሆንም የእግዚአብሔር ቃል እውነተኛና ለዘላለም የሚኖር ነው (ኢሳ. 40፡6–8)

ሁለተኛው ድምፅ በሰው ልጅና በእግዚአብሔር ቃል መካከል ያለውን ልዩነት ይገልጻል። የሰው ልጅ ተራ ገበሬም ይሁን ንጉሥ እንደ ሣር ወይም አበባ ጊዜያዊ ነው። ሰው በምድር ላይ የሚኖረው ሕይወት ለተወሰኑ ጥቂት ዓመታት ነው። በሚኖርበትም ጊዜ ሕይወቱ የሚለዋወጡና አስተማማኝነት የሌለው ነው። በተነጻጻሪነት የእግዚአብሔር ቃል ከትውልድ ትውልድ እየፈሰሰ ይኖራል። አያረጅም፤ ፋሽኑ አያልፍም፤ ወይም ውጤታማነቱ አይቀንስም። ይህ ድምፅ አለቦታው የገባ ይመስላል። እግዚአብሔር እዚህ ጋ ሕዝቡን ለማስተማር የሚፈልገው ምንድን ነው? ሦስት ዐበይት ትምህርቶች አሉ።

<u>በመጀመሪያ፥</u> እግዚአብሔር የምድር ላይ ሕይወት ከዘላለም ጋር ሲነጻጸር በጣም አጭር እንደሆነ ለሰዎች ለማስገንዘብ ይፈልጋል። ስለሆነም ሰዎች ለዛሬው ዕለታዊ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለዘላለም በመዘጋጀት መኖር አለባቸው። አይሁዶች ከስደት ወይም ከባርነት ለማምለጥ በምድር ላይ የተመቻቸ ሕይወት ለመምራት መፈተናቸው አይቀርም። ነገር ግን በምድር ላይ ሕይወታቸው አጭር እንደሆነችና የዘላለሙ ዘመን እየደረሰ እንደሆነ ተገልጸላቸዋል። ስለሆነም በምድራዊ ጊዜያዊ ሕይወት ሳይሆን በዘላለም ሕይወት ላይ ተመሥርተው ሊኖሩ ይገባል። ሰይጣን ሰዎች እንደማይሞቱና ወደፊት በሚኖራቸው ረዥም ዘመን ውስጥ እግዚአብሔርን መከተል እንዳለባቸው ወይም እንደሌለባቸው ሊወስኑ እንደሚችሉ

ይነግራቸዋል። ሰይጣን ሰዎች ለስግብግብ ፍላጎታቸው እንዲኖሩ ይፈትናቸዋል። በመሆኑም ሰዎች የእግዚአብሔር እስትንፋስ በየትኛውም ወቅት ሊነፍስባቸውና ሕይወታቸው ሊያከትም እንደሚችል ይዘነጋሉ።

<u>ሁለተኛ</u>፥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ስለነበሩበት ትክክለኛ ሁኔታ አስገንዝቦአቸዋል። ይኸውም እንደ ሣር ጊዜያዊና በሥነ ምግባራቸውም የዘቀጡ መሆናቸውን ነው። ስለሆነም የሚኩራሩበት ምክንያት የላቸውም። የባቢሎንና የአሦር ነገሥታት እንኳ እግዚአብሔር በሚፈልግበት ጊዜ የቅጣትን ነፋስ ልኮ ዝቅ የሚያደርጋቸው ሣሮች ናቸው። ምንም እንኳ እኛ ሀብታምና ድሃ፥ የተማረና ያልተማረ፥ መሪና ጭፍራ፥ ወንዶችና ሴቶች እያልን ሰዎችን በመካፋፈል አንዳንዶችን ከፍ ከፍ እያደረግን ሌሎችን ዝቅ ዝቅ ብናደርግም፥ እግዚአብሔር ግን እንዲህ አያደርግም። ምድራዊ የሰዎች ክፍፍል እግዚአብሔርን አያስደስተውም። በምድር ላይ ምንም ዓይነት ስፍራ ቢኖረን በእግዚአብሔር ዓይን ፊት የምንመካበት ምንም ነገር የሌለን ሣሮች ነን።

<u>ሦስተኛ</u>፥ እግዚአብሔር ሕዝቡ በቃሉ ውስጥ የሚገኙ የተስፋ ቃሎች ዘላለማዊ መሆናቸውን እንዲገንዘቡ ፈልጎአል (ማር. 13፡31 አንብብ)። በምርኮ የነበሩት አይሁዶች ለሁለት ትውልዶች ያህል ከኢየሩሳሌም ውድቀት በኋላ ይኖሩ ነበር። የአባቶቻቸውንና የአያቶቻቸውን ሞት ተመልክተዋል። አሁንም ቢሆን እግዚአብሔር እንደ ኢሳይያስ በመሳሰሉት ነቢያት የሰጠው የተስፋ ቃል እንደሚፈጸም የሚያመለክት መረጃ አልነበረም። ተስፋ ከማድረግ ሊቆጠቡ ተፈትነው ነበር። «እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን አይጠብቅም። አባቶቻችን እግዚአብሔር ጸሎታቸውን ሳይመልስ ሞተዋል» ብለው ሳይሟገቱ አልቀሩም። እግዚአብሔር ግን አንድ አስፈላጊ እውነት ገለጠላቸው። የሰው ልጆች ሕይወት አጭር ቢሆንም የእግዚአብሔር ቃል ግን ጊዜያዊ አይደለም። እንደ ዘላለማዊ ባሕርዩ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል ማከተሚያ የሌለው ነው። የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች እንደ ሰው ልጆች ጊዜ የሚያልፍባቸው ወይም የሚደክሙ አይደሉም። ይልቁንም ለዘላለም ይኖራሉ። ደካሞቹ የሰው ልጆች ሊያደርጉት የሚገባው የእግዚአብሔር ቃል እስኪፈጸም ድረስ መጠበቅ ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ ተስፋ መቁረጡና በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት መጣሉ ትክክል አይደለም። ይህ ካልሆነ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተጠቀሱትን ፍርዶች ለመጋፈጥ ይገደዳሉ።

4ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ዛሬ ለክርስቲያኖች እነዚህን ሦስት ትምህርቶች ማስታወሱ ጠቃሚ የሚሆነው እንዴት ነው? ለ) ሁልጊዜም እነዚህን እውነቶች በማስታወስ ቢኖሩ ሕይወታቸው እንዴት ሊለወጥ ይችላል?

ሐ. ሦስተኛ ድምፅ፡ ተዋጊው/እረኛው እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊያድን እየመጣ ነው (ኢሳ. 40፡9–11)

ሦስተኛው ድምፅ የእግዚአብሔርን ነፃ አውጭነት መልካም ዜና የሚያውጁ ሰዎች የድል ድምፅ ነው። በዚህ ጊዜ ተናጋሪዎቹ ጽዮን ወይም በኢየሩሳሌም ውስጥ የሚኖሩ ሕዝበ እግዚአብሔር እንደሆኑ ተገልጸአል። ጽዮን የነጻነት ዜናዋን አንዴ ከሰማች በኋላ ለሌሎች የጌታን መምጣት የምታውጅ የሰላም መልእክተኛ ሆነች። (አንዳንድ ትርጉሞች ጽዮን ዜናውን እንደተቀበለችና መልእክት አምጭው እንደማይታወቅ አድርገው አቅርበዋል።) የታወጀው ከታላቅ ተራራ ላይ በመሆኑ ማንም ሰው ሊሰማ ይችላል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ነፃ ለማውጣት የመምጣቱ የተስፋ ቃል የተረጋገጠ በመሆኑ ቀደም ሲል ጉብኝቱ የተፈጸመ መስሎ ተገልጸአል። ለአይሁዶች ይህ የምሥራች የፋርስ ንጉሥ የሆነው ቂሮስ ወደ አገራቸው ተመልሰው በዚያ ሊኖሩ እንደሚችሉ ማወጁ ነበር። ቤተ መቅደሱን ዳግም አንጸው ስደት ይደርስብናል ብለው ሳይፈሩ እንደ ልማዳቸው እግዚአብሔርን ሊያመልኩት ይችሉ ነበር። እግዚአብሔር እንደ ተዋጊ ባቢሎንን አሸንፎአታል። በአሕዛብ ላይ ታላቅ ኃይል ስለነበረው ሕዝቡ ወደ አገራቸው ይመለሱ ዘንድ የነገሥታትን ልብ አንቀሳቅሶአል። እግዚአብሔር በኃይል በሚሠራበት ጊዜ በታማኝነት የተከተሉትን አይሁዶች ይሸልማል። በድል ወደ ይሁዳ ምድር ይመልሳቸዋል። እግዚአብሔር እረኛ አምላክም በመሆኑ በፍቅርና በታላቅ አሳቢነት የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደተንከባከበው እንደ ንጉሥ ዳዊት ይንከባከባቸዋል።

ለክርስቲያኖች የኢየሱስ ክርስቶስን መልካም የምሥራች በዓለም ሁሉ የሚያዳርሱ ሰዎች ምን ያህል የተባረኩ እንደሆኑ ይህ ጥቅስ ያሳያል (ሮሜ 10፡8–15 አንብብ)። ተዋጊው ኢየሱስ ሰይጣንን አሸንፎታል። ከኃጢአትና ከሰይጣን ባርነት አውጥቶ ነጻነትን አጎናጽፎናል። እግዚአብሔር ለዚህ የነፃ ማውጣት መልእክት አምንታዊ ምላሽ የሚሰጡትንና እርሱን የሚከተሉትን ሰዎች ይሸልማል። እንዲሁም ይህንን የእግዚአብሔርን የነፃ አውጭነት መልእክት በዓለም ሁሉ የሚያዳርሱትን ሰዎች ያከብራቸዋል።

5ኛ ጥያቄ፡– ሀ) የእግዚአብሔርን ቃል በማወጅ ተግተው በመሥራታቸው በእግዚአብሔር ፊት እግሮቻቸው እንዳማሩ የምታውቃቸውን ሰዎች ዘርዝር። ለ) አንተ እንደምታስበው እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያንህን እግሮች የሚያየው እንዳማረ ነው ወይስ አይደለም? ግለጽ። ቤተ ክርስቲያንህ በዓለም መልካሙን ዜና ለማሰራጨት ምን እያደረገች ነው? ሐ) ከዚህ በበለጠ እንዴት ልታካሂድ ትችላለች?

በመጨረሻው ዘመን ይህ ትንቢት ሙሉ ለሙሉ ይፈጸማል። እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ አጥፍቶ ክፋት የሌለበትን መንግሥት የሚመሠርትበት ዘመን ይመጣል። የእግዚአብሔር ኃያል ክንድ (እግዚአብሔር በኃይል እንደሚሠራ የሚያመለክት የዕብራውያን አገላለጽ) ዘላለማዊ የሰላም መንግሥት ይመሠርታል። በታማኝነት ለታዘዙት የፍጻሜ ሽልማትን ሲያጎናጽፍ፥ ባለማቋረጥ ለተቃወሙት ደግሞ የፍጻሜ ፍርድን ያከናንባል። የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት የመምጣቱ ዜና ለምድር ሁሉ የምሥራች ይሆናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት የእግዚአብሔር ፍቅር እጅግ ግልጽ ማብራሪያዎች አንዱ በኢሳይያስ 40፡11 ይገኛል። ይህም በጎችን ማሰማራት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ላለው ግንኙነት ዋነኛ መግለጫ ከሆነበት የዕብራውያን ባሕል የተገኘ ነው። እረኞች አንዳንድ ጊዜ በጎቻቸውን በበትርና ድንጋይ ከሚመቱበት የኢትዮጵያ ባሕል በተቃራኒ የዕብራውያን እረኞች ከበጎቻቸው ጋር እጅግ የቀረበ ግንኙነት ነበራቸው። እረኛው ለእያንዳንዱ በግ ልዩ ስም ይሰጠዋል። እያንዳንዱ በግ የእረኛውን ድምፅ ያውቀዋል (ዮሐ. 10)። የአይሁድ እረኞች ለበጎቻቸው ከፍተኛ ፍቅር ስላላቸው የእያንዳንዱን በግ ባሕርይ፥ ብርታትና ድክመት፥ መቁሰልና አለመቁሰል፥ ወዘተ... ያውቃሉ። ገና በግልገልነት ደረጃ ያለው በግም እረኛው በጎችን ወደ ሣር ወይም ውኃ በሚያሰማራበት ጊዜ ቢደክምበት አንሥቶ ይታቀፈዋል ወይም ይሸከመዋል። ወይም ደግሞ የሚያስቸኩል ነገር ከሌለ በግልገሎቹ ፍጥነት በቀስታ እንዲሄዱ ያደርጋል። እረኛው ከትልልቆቹ በጎች ጋር እኩል እንዲሄዱ አያባረረ ግልገሎቹን አያጣድፍም።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንዲህ ዓይነት እረኛ ይሆናል። እያንዳንዱን ሰው በግል ያውቀዋል። ድካማቸውንና ብርታታቸውን ይገነዘባል። እያንዳንዱን በግ በእኩል ደረጃ አያስተናግድም። በእምነት የደከሙትን ወይም ያልበሰሉትን እየተሸከመ የሕዝቡን መንጋ የሁሉም ጉድለት በሚሟላበት አኳኋን ይመራል። ከምርኮ የሚወጡ አይሁዶች ከባቢሎን እስከ ኢየሩሳሌም ረዥም መንገድ መጓዝ ነበረባቸው። በዚህም ጊዜ የእግዚአብሔር ልዩ ጥበቃ ይደረግላቸዋል። ነገር ግን እኛም ካመንንበት ጊዜ አንሥቶ እግዚአብሔር ወደ ሰማይ ቤቱ እስኪጠራን ድረስ በሚኖረን ጉዞ ያንኑ የፍቅር እንክብካቤ እንገነዘባለን።

6ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ከዚህ ክፍል ከእግዚአብሔር ጋር ስላለን ግንኙነት ምን እንማራለን? ለ) በእግዚአብሔር ፊት በጥንቃቄ እንድንኖር ሊያስጠነቅቁን የሚገባቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው? ሐ) በደከምንና ትግል በሚበዛብን ወቅት ሊያበረታቱን የሚገባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው?

3. ይሁዳ የምትጽናናበት ሦስተኛው ምክንያት፡ የይሁዳ አምላክ ጠንካራና ዓለምን ሙሉ ለሙሉ እየተቆጣጠረ ስለሆነ (ኢሳ. 40፡12–26)

እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማጽናናት የፈለገበት የመጀመሪያው ዐቢይ መንገድ በእነርሱ ፈንታ እንደሚሠራ ማረጋገጥ ነበር። የቅጣት ዘመናቸው ያከተመ በመሆኑ እግዚአብሔር ከምርኮ መልሶ ወደ ይሁዳ ይወስዳቸዋል። እግዚአብሔር አይሁዶችን ለማጽናናት የፈለገበት ሁለተኛው መንገድ ባሕርዩን ማመልከት ነበር። «የእግዚአብሔር ስም የጸና ግንብ ነው፤ ጻድቅ ወደ እርሱ ሮጦ ከፍ ከፍ ይላል» (ምሳሌ 18፡10)። ስለሆነም የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማወቁ ክርስቲያን ግራ መጋባትና ኃዘን ባየለበት ወቅት ሊያገኝ ከሚችላቸው ታላላቅ ዋስትናዎች አንዱ ነው። በቀጣዮቹ ሁለት ቁጥሮች ኢሳይያስ በችግር ጊዜያት በእምነታችን እንድንጸና ለማበረታታት በመፈለግ ስለ እግዚአብሔር ባሕርያት ብዙ ነገሮችን ገልጾልናል።

አይሁዶች በምርኮ ላይ ሆነው የተመለከቷቸው አማልክት ሁሉ ሰው ሠራሽ ነበሩ። አንዳንዶች በባርነት በተቀመጡባቸው ቤቶች ጥግ ተቀምጠው ነበር። ሌሎች ደግሞ ታላላቅና በግሩም ሁኔታ ተቀርጸው በአብያተ ጣዖታት ይቀመጡ ነበር። ለእነዚህ ጣዖታት የአይሁዶች ምላሽ ምን ነበር? እነዚህን ጣዖታት አይተዉት ከማያውቁትና ጣዖት ካልተሠራለት ከእግዚአብሔር ጋር የሚያነጻጽሩት እንዴት ነው? እግዚአብሔር በሰዎች እጅ ከተሠሩት ጣዖታት እንዴት እንደሚለይ ሕዝቡ እንዲያውቁ አጥብቆ ይፈልግ ነበር። ጣዖታቱ ከታላላቅ ሀውልቶች ወይም ከሰዎች አሳቦች መሠራታቸው ለውጥ አልነበረውም። ስለሆነም ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር ታላቅነት ባቀረባቸው ተከታታይ ጥያቄዎችና መግለጫዎች በእውነተኛ ሕያው አምላክና በሌሎች አሕዛብ አማልክት መካከል ያለውን ልዩነት በግልጽ አስቀምጦአል።

ሀ. ፈጣሪው እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ በመሆኑ ፍጥረትን በእጁ ይይዛል (ኢሳ. 40፡12)

ኢሳይያስ የጀመረው ተከታታይ ጥያቄዎችን በማቅረብ ነው። የእነዚህ ጥያቄዎች የእያንዳንዳቸው መልስ «እግዚአብሔር» መሆኑ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር የዓለም ፈጣሪ ነው። በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ እግዚአብሔር ቃልን በመናገሩ ምክንያት ዛሬ በምድር ላይ ያለው ሁሉ ወደ መኖር እንደመጣ እናነባለን። ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ከፈጠራቸው ነገሮች ጋር ያነጻጽረዋል። የጀመረው በውኃ ነው። የዓለም ሁለት ሦስተኛው እጅ ከውኃ የተሠራ ነው። በጀልባዎች ለማቋረጥ የሳምንታትን ጊዜ የሚጠይቁ ግዙፍ ውቅያኖሶች አሉ። እግዚአብሔር ግን እጅግ ታላቅ በመሆኑ ያንን ሁሉ ውኃ

በእፍኙ የሚሰፍር ይመስላል። ከመሬት በላይ ከዋክብትና ሌሎች ሥርዓተ ፀሐያት የሚፍለከለኩባቸው ሰማያትስ? ብዙ ቢሊዮን ማይሎች ርቀው ለማየት በሚችሉ ቴሌስኮፖች አማካኝነት ሳይንቲስቶች እንደተመለከቱት ከሰዎች እይታ ባሻገር እንደኛው ዓይነት በርካታ ሥርዓተ ፀሐያት አሉ። በመሠረቱ የሰማያትን ዳርቻ የሚያውቅ የለም። ኢሳይያስ አጽናፈ ዓለሙ ምንም ያህል ግዙፍ ቢሆን እግዚአብሔር በስንዝሩ እስከሚለካው ድረስ ከዚያ እንደሚበልጥ ገልጾአል። በዓለም ላይ የሚገኘው አፈርስ? አንዲት ትንሽ ኮረብታ ለማፈራረስና ቆሻሻውን ለማስወገድ ትላልቅ መኪናዎች ለረዥም ሰዓታት ሲሠሩ ይውላሉ። በዓለም የሚገኘው ቆሻሻ ከእግዚአብሔር ኃይል ጋር ቢነጻጸር በትንሽ ቅርጫት ውስጥ እንደተያዘ ያህል ነው። የደቡብ ኢትዮጵያ ታላላቅ ተራሮች፥ የሂማላያ ተራሮች፥ አልፕስ፥ ወዘተ... ከእግዚአብሔር የበለጡ ናቸውን? አይደሉም! አንድ የመደብር ነጋዴ ብርቱካኖችን በአንድ በኩል አነስተኛ ድንጋዮችን በሌላ ወገን አድርጎ እንደሚመዝን ያህል ትናንሽ ናቸው። ስለሆነም እግዚአብሔርን ከየትኛውም ፍጥረቱ ጋር ብናነጻጽር ሁሉንም የሚቆጣጠር ታላቅ አምላክ እንደሆነ እንረዳለን። እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ የሚቆጣጠር ከሆነ ከችሎታው የሚበልጥ ምንም ነገር እንደሌለ እንረዳለን። ሕዝቡ በቀላሉ ከምርኮ ወይም ከችግሮቻቸው እንዲያመልጡ ሊያደርግ ይችላል።

ለ. የሁሉን አዋቂው አምላክ ሥራዎች ፍጹም በመሆናቸው የማንም ጥበብ አያስፈልጋቸውም (ኢሳ. 40፡13–14)

በቀጣዮቹ ተከታታይ ጥያቄዎች ኢሳይያስ የሚጠብቀው ምላሽ «ማንም!» የሚል ነው። ሳይንቲስቶች ለብዙ ምእተ ዓመታት የእግዚአብሔርን ፍጥረት ሲያጠኑ በመቆየታቸው ዓለም እንዴት እንደተጋጠመች የሚያስረዳውን ምሥጢር ሁሉ ያወቁ ይመስላቸዋል። የፍጥረትን እንቆቅልሽ ከተገነዘቡ የእግዚአብሔርን ያህል እውቀትና ኃይል እንደሚኖራቸው በማሰብ ለብዙ የተለያዩ ነገሮች ንድፈ አሳቦችን ይዘው ይመጣሉ። ይሁንና፥ የእግዚአብሔር ጥበብ ከሰው ጋር የሚነጻጸረው እንዴት ነው? አንድ ሰው ከእግዚአብሔር የበለጠ እውቀት በማግኘት እግዚአብሔር ለሕዝቡ የወጠናቸውን ዕቅዶች ያፈርሳል ብለን መስጋት አለብን? የባቢሎን ጠቢባን ከእግዚአብሔር ይልቃሉን? ወይስ የአሜሪካ፥ ወይም የሩሲያ፥ ወይም የኢትዮጵያ መሪዎችስ? በፍጹም! በዓለም እጅግ ጠቢብ የተባለው ሰው እንኳ የእግዚአብሔርን ዕቅዶች ሊረዳ አይችልም። ይህ እግዚአብሔር በአንድ ሁኔታ ውስጥ የሚሠራውን ነገር አውቃለሁ እንዳንል ሁላችንንም ሊያስጠነቅቀን ይገባል። አዋቂው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር በቃሉ ካልገለጸልን በስተቀር የእግዚአብሔር አሳብ ምን

እንደሆነ አናውቅም። የእግዚአብሔርን አሳብ የሚያውቅ ስለሌለ ዕቅዶቹን ለማከሸፍ የሚያስችል መላ ሊመታ የሚችል አይኖርም። የእግዚአብሔር ጥበብ የግሉ በመሆኑ በሌሎች የተፈጠሩ ነገሮች ላይ አይደገፍም። በመላእክት ወይም በሰው ልጆች ላይ አይደገፍም። አማካሪ አያሻውም። (ይህ ዓለምን በፈጠረበት ጊዜ የሌሎችን አማልክት ምክር እንደጠየቀ ከሚነገርለት ማርዱክ ከተባለው የባቢሎናውያን ጣዖት የተለየ ነው።) እግዚአብሔር ሁሉን ስለሚያውቅና ከሁሉም የተሻለውን መንገድ ስለሚረዳ የጠቢባንን ምክር አይሻም። እናም ሁልጊዜ የተሻለውን መምረጥ ይችላል። እግዚአብሔር አንድን ነገር ለመማር ወደ ትምህርት ቤት መሄድ አላስፈለገውም። እንዲያውም እግዚአብሔር የሚማረው አዲስ ነገር የለውም። ከዘላለም ዘመናት በፊትና ከዘላለም ዘመናት በሁዋላ የእግዚአብሔር እውቀት ሁልጊዜም ሙሉ ነበር። ለዚህ ነው እያንዳንዳችንን ከዓለም ፍጥረት በፊት ሊያውቀን የሚችለው (ኤፌ. 1፡4)። እኛን ከመፍጠሩ በፊት ስለ እኛ ሁሉንም ነገር ያውቅ ነበር። እናምን እንደሆነ ወይም አናምን እንደሆነ፥ ወዘተ... ያውቅ ነበር። ይህ ማንም ሰው የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንደማያጥፍና ወደ አገራቸው እንደሚመለሱ በማስገንዘብ አይሁዶችን ያጽናና ነበር። ዛሬም ደግሞ የእግዚአብሔርን ዕቅድ ማንም እንደማይረታ በመረዳት በርኃታ ልንቀመጥ እንችላለን። የመንግሥት ሕግጋት ከእግዚአብሔር የተሰወሩ ባለመሆናቸው የእግዚአብሔርን ዕቅዶች የሚያጥፉ አይሆኑም። እንዲያውም እግዚአብሔር ዓላማውን ለማሳካት ይጠቀምባቸዋል።

7ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ከእግዚአብሔር የቁጥጥር ዓቅም በላይ የሚመስል ነገር በአንተ ላይ የተፈጸመበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ለመጠራጠር የተፈተንኸው እንዴት ነው? ሐ) በእነዚያ ጊዜያት የእግዚአብሔርን ኃይልና ጥበብ በግልጽ መረዳትህ በእምነትህ እንድትጸና ያደረገህ እንዴት ነው?

ሐ. ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔር የዓለምን አገሮች ሁሉ ይቆጣጠራል (ኢሳ. 40፡15–17 አንብብ)

ዓለምን በሰብዓዊ ዓይኖች በምንመለከትበት ጊዜ የአንዳንድ አገሮች ኃያልነት ያስደንቀናል። አሦርና ባቢሎን፥ በኋላም ፋርስና ሜዶን አይሁዶችን በኃያልነታቸው አስደምመዋቸው ነበር። ዛሬ ደግሞ አሜሪካ ወይም ሩሲያ ኃያላን አገሮች ናቸው። የኢትዮጵያ መንግሥትም እንኳ በዓቅሙ ኃያልነቱን ሊያሳየን ይችላል። እነዚህን አገሮች በተለይም የእግዚአብሔርን ሕዝብ በትጋት የሚዋጉትን አገሮች በምንመለከትበት ጊዜ ለክርስቲያኖች በፍርሃት መራዱ ቀላል ነው። የመንግሥታት መሪዎች ሕይወታችንን ስለሚቆጣጠሩ የሞትና የሕይወት ሥልጣን በእጃቸው የሚገኝ ሊመስለን ይችላል። በዚህ

ዓይነት ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ወዴት ነው? የበለጠ ኃይል ያለው እግዚአብሔር ነው ወይስ የሚገዙን መንግሥታት? የሃይድሮጅንና የአተም ቦምቦችን ይዘው በጀቶች የሚዋጉ የሰው ልጆች ሠራዊት ከእግዚአብሔር ቁጥጥር ውጭ ናቸውን? ኢሳይያስ እንደሚለው የዓለም አገሮች ሁሉ ወታደሮች ቢሰባሰቡና ወታደራዊ ኃይላቸውን በእግዚአብሔር ላይ ቢያወርዱ ተግባራቸው በውኃ ከተሞላው ገንቦ ውስጥ አንድ ጠብታ ከመጨመር አይልቅም። ጠብታው ውኃ በገንቦው ውስጥ ላለው ትልቅ ውኃ ለውጥ ያመጣ ይሆን? አያመጣም! ወደ ሱቅ ሄደህ ከመመዘኛ ድንጋዮች ላይ አዲራ ብትመለከት? በአዲራው ምክንያት ሚዛኑ እየተዛባ ነው ብለህ ለነጋዴው አቤቱታ ታቀርባለህ? አታደርገውም! የዓለም አገሮች ኃይልም በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ ላይ የሚያስከትለው ለውጥ አይኖረውም። ከአምላካችን ታላቅነት ጋር ሲነጻጸሩ የዓለም መሪቶችና ደሴቶች የጎላ ሚና የላቸውም። እንዲያውም እነዚህ አገሮች ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጻጸሩ ከቁጥር የማይገቡ በመሆናቸው ከምናምን የሚያንሱ ከንቱ ነገሮች ናቸው። በሒሳብ ቋንቋ ‹ኔጌቲቮች› ወይም ከዜሮ በታች መሆናቸውን ልንገልጽ እንችላለን።

ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለማሳየት የሊባኖስን ምድር በምሳሌነት ተጠቅሞአል። ኢሳይያስ በሰዎች ሃይማኖታዊ አምልኮ ላይ ትኩረት አድርጎአል። እግዚአብሔር የሰውን ልጅ አምልኮ ሳያገኝ መኖር አይችልም? ሕልውናው የተደገፈው በሰዎች አምልኮ ላይ ነው? የሰው ልጅ እግዚአብሔርን እንደሚገባው ሊያመልከው ይችላል? ኢሳይያስ የብሉይ ኪዳንን የአምልኮ ሥርዓት በመጠቀም የዓለም እንጨቶችና እንስሳት ሁሉ ለእግዚአብሔር ማንነት የሚገባውን አምልኮ ሊያቀርቡለት እንደማይችሉ ገልጾአል። ሊባኖስ በግዙፍ ደኖቹና በትላልቅ የዝግባ ዛፎቹ የታወቀ እንደሆነ ቀደም ሲል ተመልክተናል። እንስሳትም እንዲሁ በብዛት ይገኙበታል። የሊባኖስ እንጨቶች ሁሉ ተቆርጠው መሠዊያ ቢሠራና በአገሪቱ የሚገኙ እንስሳት ሁሉ ተገድለው ለመሥዋዕትነት ቢቃጠሉ፥ ይህ ለእግዚአብሔር ታላቅነት በቂ መግለጫ ይሆናል? አይሆንም! እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ በመሆኑ በዓለም የሚገኙ እንጨቶችና እንስሳት ሁሉ ለታላቅነቱ የሚገባውን ክብር ለማምጣት አይችሉም።

8ኛ ጥያቄ፦ ሀ) መንግሥት ከእግዚአብሔር የበለጠ ኃይል ያለው የመሰለበትን ሁኔታ ጻፍ። ለ) ታሪክ እግዚአብሔር ከመንግሥታት እንደሚበልጥ ያሳየው እንዴት ነው? ሐ) እግዚአብሔር መንግሥታትን መቆጣጠሩ የሚያበረታታህ እንዴት ነው?

መ. የማይታየው እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ከንቱ ጣዖታት የላቀ ነው (ኢሳ. 40፡18–20 አንብብ)

በምርኮኛነታቸው ዘመን አይሁዶች ባለማቋረጥ ከጣዖታት ጋር ይጋፈጡ ነበር። በባርነት በሚኖሩባቸው ስፍራዎችም ሆነ በአብያተ ጣዖታት ሁሉ ይኸው ሁኔታ ያጋጥማቸዋል። ይህም እውነተኛው አምላክ የማይታየው እግዚአብሔር ይሆን ወይም የሚመለኩቷቸው ጣዖታት መሆናቸውን ለመረዳት ግራ እንዲጋቡ ያደርጋቸዋል። አይሁዶች በምርኮኛነታቸው ወቅት የእውነተኛ አምላክ አምልኮአቸውን መቀጠል የሚችሉት እንዴት ነበር? ቁልፉ ነገር በሕያው እግዚአብሔርና ሰዎች በሚያመልኳቸው ጣዖታት መካከል የሚገኘውን ልዩነት መረዳታቸው ነበር።

በመቀጠልም ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ከምን ጋር እንደምናወዳድረው ጠይቋል። መልሱ «ከምንም!» የሚል ነው። የሰው ልጅ ምስል የሌለውንና የማይታየውን ነገር ለማምለክ ይቸገራል። ሰዎች የእግዚአብሔርን ታላቅነት አይተው ወደሚረዱት ነገር ዝቅ ለማድረግ ይፈልጋሉ። በጥንት ዘመን ዛሬ በሕንድ አገር እንደሚደረገው የጣዖት ምስል ቀርጾ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለማሳየት መሞከር የተለመደ ነበር። በሌሎች ስፍራዎች ሰዎች እግዚአብሔርን ይበልጥ ለመረዳት በሚችሉባቸው መንገዶች ያስባሉ። ክርስቲያኖች ለመጸለይና ለማምለክ ይረዳቸው ዘንድ በቤታቸው ወይም በቤተ ክርስቲያናቸው የኢየሱስ ክርስቶስን ምስል ማስመቀመጣቸውም እንደዚሁ የተሳሳተ ተግባር ነው። ሁልጊዜም ስለ እግዚአብሔር በምናስብበት ጊዜ በማይመጠን ዓይነት ሁኔታ ከእኛ የተለየ መሆኑን በመገንዘብ እርሱን ከውስን ነገር ጋር ከማነጻጸር ልንታቀብ ያሻል። አእምሮአችን እግዚአብሔር እንደኛው ነው ብሎ እንዲቀበል ካደረግን እውነተኛውን ዘላለማዊ አምላክ ሳይሆን ጣዖት ማምለክ እንጀምራለን።

እግዚአብሔር የማይታይ አምላክ በመሆኑ ምን እንደሚመስል የሚያውቅ ሰው የለም። ምንም እንኳ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውም አምላክም መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን ዓይነት አካላዊ ገጽታ እንደነበረው የሚያመለክት ነገር የለም። ማንኛውም ሰው–ሠራሽ የእግዚአብሔር ምስል በውስን የሰው ልጅ አስተሳሰብ የተቀረጸ እንደመሆኑ የእግዚአብሔርን ታላቅነት በተሟላ መልኩ ሊገልጽ አይችልም። ስለሆነም እግዚአብሔርን እንደ መሳደብ ነው። እግዚአብሔርን ሰው በሚሠራው ወይም በሚያስበው በማንኛውም ነገር ማወዳደር አይቻልም።

ስለሆነም እግዚአብሔር ጣዖታት ምን ያህል ጣዕም እንደሌላቸውና እነርሱን ማምለኩ ደግሞ ምን ያህል ከንቱነት እንደሆነ አይሁዶች

እንዲገነዘቡ ፈለገ። ይህንንም አሳብ ጣዖታት በሚሠሩበት ጊዜ የሚሆነውን ሁኔታ በማብራራት ገለጸላቸው። ሀብታም ሰው በወርቅ የተለበጠ የእንጨት ጣዖት ሲሠራ፥ የገንዘብ ዓቅሙ ያልፈቀደለት ድሀ ግን የማይነቅዝ እንጨት ፈልጎ ይቀርጻል። ጣዖቱ ምንም ያህል የከበረ ወይም የዘቀጠ ቢሆንም ሁልጊዜም የሚሠራው እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ነገሮች ነው። ይህም ከፈጣሪው አምላክ እጅግ ያነሰ ያደርገዋል። እንዲህ ዓይነቱ ጣዖት ይረዳኛል ብሎ ማሰቡ ምን ያህል ጅልነት ነው! እግዚአብሔር ከሰው ልጅ አእምሮ በላይ የገዘፈ አምላክ በመሆኑ ከእርሱ ጋር የሚነጻጸር ነገር ከቶውንም ሊኖር አይችልም!

9ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ሰዎች እግዚአብሔርን በሰብአዊ ገጽታ ለማሰብ የሚፈተኑባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? የእግዚአብሔርን ጣዖት የመፍጠር ያህል የተሳሳተ አሳብ ልንይዝ የምንችለው እንዴት ነው? ይህ የእግዚአብሔርን ባሕርይ በትክክል ስለመረዳትና ይህንኑ ለቤተ ክርስቲያናችን ምእመናን ስለማስተማር አስፈላጊነት የሚያስተምረን ምንድን ነው? ለ) ብዙ ክርስቲያኖች የኢየሱስ ክርስቶስን ምስል በቤታቸው ወይም በቤተ ክርስቲያናቸው የሚሰቅሉት ለምንድን ነው? ይህ አደገኛ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው? ሐ) የእግዚአብሔርን ባሕርይ አስመልክቶ ግንዛቤአችንን ለመቅረጽ መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ መጠቀም አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

ሠ. እግዚአብሔር አጽናፈ ዓለሙንና የአሕዛብ መሪዎችን በፍጹማዊ ኃይሉ ይቆጣጠራል (ኢሳ. 40፡21–24 አንብብ)

እግዚአብሔር ከዘመናት ጅማሬ ጀምሮ ለሕዝቡ ለማስተማር ከፈለጋቸው እውነቶች መካከል አንዱ ስለ ታላቅ ኃይሉ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለ ማንነቱ በሁለት መንገዶች ለማስተማር እንደፈለገ ይናገራል። <u>በመጀመሪያ</u>፥ ፍጥረት ራሱ የእግዚአብሔርን ክብርና ታላቅነት የሚናገር መሆኑ ተገልጾአል (መዝ. 19፡ ሮሜ 1፡19–20)። ሁለተኛ፥ በነቢያት አማካኝነት በተሰጠው ቃሉ አማካኝነት እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል በግልጽ ተመልክቶአል። ኦሪት ዘፍጥረት የፍጥረትን ታሪክ በመናገር የሚጀምረው ለዚህ ነው። እንዲህ ዓይነቱን ታላቅ ፍጥረት በቀላሉ ሊያስገኝ የሚችለው ታላቅ፥ ኃያልና ከሌሎች ጋር ሊነጻጸር የማይችል አምላክ ብቻ ነው። ለዚህ ነው እግዚአብሔር ለሙሴ እርሱን የሚወክል ምንም ዓይነት ምስል እንዳይሠሩ የከለከለው። ሰው የሚሠራው የትኛውም ነገር እግዚአብሔርን በትክክል ሊወክለው አይችልም። እግዚአብሔር ባለማቋረጥ ስለ ራሱ ለሰዎች ለመግለጽ የሞከራቸው እውነቶች አሉ።

1. እግዚአብሔር ከምድር ከፍ ቢልም ምድርን አቅፎ ይዟል። በዘላለማዊ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦአል። እርሱን ከሰዎች ማነጻጸር ማለት

አንበጣዎችን ከሰዎች ጋር እንደማነጻጸር ሊቆጠር ይችላል። በምድር ላይ ከእርሱ ጋር የሚወዳደር ምንም ነገር የለም።

2. እግዚአብሔር ከሰማያት በላይ ነው። አብዛኞቹ ጥንታዊ ሃይማኖቶች ፀሐይን፥ ጨረቃንና ከዋክብትን ያመልኩ ነበር። እግዚአብሔር ግን ከእነዚህ እጅግ ይልቃል። ከመንገድ ዳር ዕቃዎችን የሚሸጥ ሰው ከፀሐይ ለመከላከል ከራሱ ላይ የፕላስቲክ ጠለላ እንደሚያደርግ ወይም ለልቅሶ ድንኳን እንደሚጣል፥ እግዚአብሔር አጽናፈ ዓለሙን ከስፍራው ያኖረው በቀላሉ ነበር።

3. እግዚአብሔር ከአገር መሪዎች በላይ ነው። እንደ ናቡከደነፆር፥ ሂትለር፥ ስታሊን፥ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ወይም ክሊንተን የመሳሰሉ ታላላቅ መሪዎች ከሥልጣን ላይ በሚወጡበት ጊዜ የሚሾማቸው እግዚአብሔር ነው። ዓላማው ከተጠናቀቀ በኋላ የሚሽራቸውም እርሱ ነው። ከመሬት ላይ ተዘርታ በማጎንቆል እንደምታድግና በኋላም በነፋስ ማዕበል እንደምትወድም የእህል ቅንጣት፥ ታላላቅ የአሕዛብ መሪዎችና መንግሥቶቻቸውም በማዕበል የሚወገዱ ጊዜያዊ ተቋማት ናቸው። ስለሆነም የእግዚአብሔር ሕዝቦች የአሕዛብ መሪዎችን፥ መንግሥቶቻቸውን ወይም ደንቦቻቸውን ሊፈሩ አይገባም። እነዚህ የእግዚአብሔር ፍርድ መጥቶ እስኪያስወግዳቸው ድረስ የሚቆዩ ጊዜያዊ ነገሮች ብቻ ናቸው።

ረ. እግዚአብሔር ከዋክብትን በቅርበት ያውቃቸዋል፤ ይጠብቃቸዋልም (ኢሳ. 40፡25–26 አንብብ)

የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለማጠናከርና ከማንኛውም ነገር በተለይም አይሁዶች በምርኮኛነት ከተወሰዱባቸው አገሮች ጣዖታት ጋር እንደማይነጻጸር ለማሳየት ኢሳይያስ ወደ ፍጥረት ተመለሰ። እግዚአብሔር አብርሃም ዓይኖቹን አንሥቶ ከዋክብትን እንዲመለከት እንደጠየቀው ሁሉ የአብርሃም ትውልዶችም እነዚያኑ ከዋክብት እንዲመለከቱ ጠየቃቸው። እጅግ ርቀው የሚታዩ በሺህዎች የሚቆጠሩ ከዋክብት ቢኖሩም እግዚአብሔር እያንዳንዱን ኮከብ ያውቀዋል። (በአይሁድ ባሕል ለአንድ ነገር ስም መስጠት በዚያ ነገር ስም አውጭው ሥልጣን እንዳለው ያመለክታል። አዳም ለዓለም ፍጥረታት ሁሉ ስም ባወጣላቸው ጊዜ እግዚአብሔር እንዲገዛቸው የሰጠውን ሥልጣን እየተጠቀመ ነበር።) እግዚአብሔር ከከዋክብት ጋር የሚያደርገው ግንኙነት የሚቀጥል ሲሆን፥ በቦታው እንዲሆን እስከፈለገበት ጊዜ ድረስ እያንዳንዱ ኮከብ እዚያው ይቆያል። ያለ እርሱ ፈቃድ የሚጎድል ኮከብ የለም። ተወርዋሪ ከዋክብት ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር የሚንቀሳቀሱ ናቸው።

በጥንት ሃይማኖቶች በተለይም አይሁዶች በምርኮኛነት በነበሩባት ባቢሎን ፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብት ይመለኩ ነበር። እግዚአብሔር ምን ያህል ታላላቅና አስደናቂዎች ቢሆኑም እነዚህ ነገሮች የፍጥረቱ አካላት ብቻ እንደሆኑ እየገለጸ ነበር። ስለሆነም ሊመለኩ አይገባም ነበር። እግዚአብሔር ሕይወት የሌላቸውን ከዋክብት በየስማቸው የሚጠራ ከሆነ፥ ልጆቹንስ ምን ያህል በየስማቸው ይጠራቸው ይሆን? ለእግዚአብሔር በእርሱ የሚያምኑ ሰዎች እንደ ከዋክብት ሕይወት ከሌላቸው ነገሮች የሚልቁ ናቸው።

10ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ከእነዚህ የእግዚአብሔር ባሕርያት ልንማር የምንችላቸውን አስፈላጊ ትምህርቶች ዘርዝር። ለ) ለክርስቲያኖች እነዚህን ባሕርያት ማወቅ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሐ) በዚህ ክፍል ውስጥ የተዘረዘሩት ባሕርያት እያንዳንዳቸው ክርስቲያኑን ሊረዱ የሚችሉበትን ሁኔታ ግለጽ።

4. ሕዝቡን በቅርበት የሚያውቀው አምላክ በችግር ጊዜ የሚያስፈልጋቸውን ብርታት የመስጠት ጥበብ አለው

(ኢሳ. 40፡27–31 አንብብ)

የአይሁዳውያኑ ሙግት «አምን፥ እግዚአብሔር ኃያል ነው። ነገር ግን የሚኖረው በጣም ርቆ በሰማይ ነው። ስለ እኔ ችግሮች አይገደውም። ባቢሎናውያን አሸንፈውናል። ጣዖታትን ለሚያመልኩት ሰዎች በባርነት ተገዝተናል። እግዚአብሔር ችግሮቻችንን አይረዳም ወይም ሊረዳን አይፈልግም» የሚል ሊሆን ይችላል።

11ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በሕይወትህ እንደዚህ ባለ ሁኔታ የተፈተንህባቸውን ጊዜያት ዘርዝር። ለ) በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ያበረታታህ እንዴት ነበር?

የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማወቁ በጣም አስፈላጊ ነው። ሆኖም ግን የእግዚአብሔር ባሕርይ በእኛ ላይ የሚያመጣውን ለውጥ መገንዘቡ የበለጠ አስፈላጊ ነው። ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ዐበይት ነጥቦችን ጠቅለል አድርጎ ካቀረበ በኋላ አይሁዶች ከነበሩበት ሁኔታ ጋር አዛምዶታል። እግዚአብሔር፥

ሀ) ሁሉንም ነገር የሚቆጣጠር ጌታ ነው።

ለ) የማያረጅ፥ የማይለወጥ፥ የማይሸነፍ ወይም የማይሞት ዘላለማዊ አምላክ ነው።

ሐ) ሁሉንም ነገር የፈጠረና የፈጠረውንም ሁሉ የሚቆጣጠር የምድር ጌታ ነው። እጅግ ርቆ የሚገኘውን የባቢሎንን ግዛት ጨምሮ እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም የማይሠራበት የምድር ክልል አልነበረም።

መ) ሁሉን ቻይ አምላክ በመሆኑ አይዝልም፤ አይደክምም። ዓለምን ከፈጠረ በኋላ እንኳ እግዚአብሔር አልደከመም። ስለሆነም

የሕዝበ እግዚአብሔር ችግር እግዚአብሔር ለማስተካከል እስከሚደክምና እስከሚዝል ድረስ ከባድ አይደለም።

ሠ) ሁሉን አዋቂ በመሆኑ ነገሮችን ሁሉ በጥልቀት ይገነዘባል። ስለሆነም ምንም የሚያስደንቀው ወይም መፍትሔ ለመስጠት የሚቸግረው ነገር የለም። የሰው ልጆች ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንገዶቹ ከፊል ግንዛቤ ብቻ ስላላቸው ሁልጊዜም በአንድ ሁኔታ ውስጥ ዓላማዎቹን ሁሉ ሊረዱ እንደማይችሉ ማጤን አለባቸው።

ነገር ግን እንደ እርሱ ሳይሆኑ ለሚደክሙ፥ ተስፋ ለሚቆርጡና ብዙ ጊዜ እምነታቸውን ለመተው ለሚፈተኑ ሕዝቦቹ የሚሰጠው የተስፋ ቃል ምንድን ነው?

1) ብርታት እንደሚሰጣቸው ቃል ይገባላቸዋል። እግዚአብሔር ሕዝቡ ከሕይወት ችግሮች የተነሣ ሊደክም እንደሚችል ያውቃል። ስለሆነም ያደርጉት ዘንድ የሚፈልገውን እንዲያደርጉና እርሱን በሚያስከብር ሕይወት እንዲኖሩ ለማድረግ ታላቅ ኃይል እንደሚሰጣቸው ይናገራል። እንዲያውም እግዚአብሔር ሕዝቡ ኃይላቸውን እንደሚያድሱ ገልጾአል። በዕብራይስጡ ቋንቋ ይህ ቃል ድካማቸውን በእግዚአብሔር ብርታት እንደሚለውጡ ያሳያል። ይህ ልብሱን አውልቆ አዲስ ስለሚለብስ ሰው የሚነገር ቃል ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር የሕዝቡን ድካም አስወግዶ የራሱን ብርታት ይሰጣል። ስለሆነም የእግዚአብሔር ሕዝብ እጅግ ውስን በሆነው ኃይላቸው ላይ መደገፍ የለባቸውም።

2) ኃይልን ይጨምርላቸዋል። በርግጥ የእግዚአብሔር ሕዝብ በድካም መዛላቸው ግልጽ ነው። ከባቢሎን ወደ ይሁዳ የሚወስደው መንገድ ሩቅ ነበር። ከመሬት ወደ ሰማይ የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ ደግሞ ከዚያ የበለጠ ሩቅ ነው። የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመንገዳቸው የሚረዳቸው ምን ይሆን? እግዚአብሔር ለሕዝቡ የራሱን ኃይል እንደሚሰጥ ተናግሮአል።

በተፈጥሮአዊ ኃይላቸው የሚመላለሱ ወጣቶች እንኳ ብዙ ከተጓዙ ወይም ቀኑን ሁሉ ሲሠሩ ከዋሉ በኋላ ይደክማሉ። እየደከሙ ሲሄዱ ተሰናክለው ሊወድቁ ይችላሉ። እግዚአብሔር ግን ሕዝቡ በጉዞው እንዲገፋበት ኃይሉን ይሰጣል። መቋቋም ብቻ ሳይሆን ችግሮቻቸውን እስከ ማሸነፍ ይደርሳሉ። ኢሳይያስ በኃይሉና በችሎታው ከታወቀው ከንስር ጋር አነጻጽሮአቸዋል። ንስር ከማንኛውም ወፍ የላቀ በመሆኑ የአእዋፋት ንጉሥ በመባል ይታወቅ ነበር። እንዲሁም ደግሞ ከማንኛውም ችግርና አደጋ ከፍ ብሎ መብረር ይችል ነበር። በአንድ በኩል ነፋስ ንስሩ ወደፈለገበት እንዳይበር እየተከላከለ ያስቸግረዋል። ነገር ግን ንስሩ ከመሬት በላይ ሳይታክት እንዲበር የሚያደርገው

ይሽው የአየር ችግር ነው። ንስሩ መብረሩን እንዲቀጥል ያደርገዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ድካማችን በእግዚአብሔር ብርታት ሲተካ በልዕለ ተፈጥሮአዊ ብርታት እንድንኖር የሚያደርጉን የምንጋፈጣቸው ችግሮች ናቸው። በእግዚአብሔር የሚታመኑ ያለድካም መሮጥና መሄድ እንደሚችሉ ኢሳይያስ ይናገራል። በሌላ አነጋገር፥ ሕይወታችን ሁሉ የተሞላው በእግዚአብሔር የማስቻል ብርታት ነው።

ነገር ግን ይህንን ብርታት የምናገኘው እንዴት ነው? ልናደርገው የሚገባን አንድ ነገር አለ? ብዙ መጾም፥ መጸለይ፥ ወይም መጮህ ይኖርብናል? እነዚህ ነገሮች ቢኖሩም እንኳ በራሳቸው የእግዚአብሔርን ኃይል አያመጡም። ኢሳይያስ የሚያድሰው ኃይል እግዚአብሔርን ተስፋ በምናደርግበት ጊዜ እንደሚመጣ ገልጾአል። እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ ማለት በእርሱ መታመን፥ ጉድለቶቻችንን እንዲሞላና ለሁኔታው የሚያስፈልገንን ብርታት ይሰጠን ዘንድ ወደ እርሱ መመልከት ማለት ነው። ይህም ትዕግሥትንና በእግዚአብሔር መታመንን አጣምሮ የያዘ ነው። አይሁዶች በምርኮ ሆነው ችግሮቻቸውን ይፈታላቸው ዘንድ በሚጸልዩበት ጊዜ ይህንኑ እንደሚያደርጉ ተገልጾላቸዋል። ወይም ደግሞ ወደ ይሁዳ እየተመለሱ በመንገድ ላይ በሚዝሉበት ወቅት ወደ እግዚአብሔር ቢመለከቱ በፊታቸው ያለውን ማንኛውንም ዓይነት እንቅፋት ለማንሣት ኃይላቸውን ያድሳል። ዛሬም ችግሮችን በምንጋፈጥበት ጊዜ እግዚአብሔር ጉድለታችንን እንዲሞላና ብርታቱን እንዲሰጠን በርጋታና በመጠባበቅ ብንጠይቀው ይህንኑ ያደርግልናል። ብዙውን ጊዜ ብርታቱን የሚሰጠን ወደ ችግሮች ከመግባታችን በፊት ሳይሆን ከችግሮቹ ውስጥ ገብተን እርዳታ በምንፈልግበት ጊዜ ነው። በራሳችን ኃይል እየሠራን ከሆነም ብርታቱን አይሰጠንም። ትግሉ አድክሞን ወደ እርሱ እስክንመለስ ድረስ ይጠብቀናል። ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ለችግሮቻችን የሚሰጠው ምላሽ ችግሮቻችንን ማስወገድ ሳይሆን እያንዳንዱ ቀን የሚያመጣውን ፈተና መቋቋም እንችል ዘንድ ኃይልን መስጠት ነው። የምንበረው የችግር ነፋሳት ስለሌሉ ሳይሆን የትግሎቻችን ነፋሳት ለመኖርና ለመሥራት የሚያስፈልገንን ኃይል ከእግዚአብሔር ዘንድ እንድንጠቀም ስለሚያደርጉ ነው። ኢሳይያስ ምንም ዓይነት ችግሮች እንደማይኖሩ አልተናገረም። ነገሩ የዚህ ተገላቢጦሽ ነው። የሚያዳክሙን ሁኔታዎች ይኖራሉ። ነገር ግን በእግዚአብሔር ከተማመንን እግዚአብሔር ድካማችንን በብርታቱ ይለውጠውና ሁሉም ሰው እርሱ በእኛ እንደሚሠራ ይገነዘባል። እግዚአብሔር ጳውሎስን እንዳስተማረው፥ «ጸጋዬ ይበቃሃል፤ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና» (2ኛ ቆሮ. 12፡9)።

12ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ለአካላዊና መንፈሳዊ ዝለት የዳረጉህን አንዳንድ ሁኔታዎች ጠቃቅስ። ለ) በራስህ ብርታት በታገልህ ጊዜ ምን ተከሰተ? ሐ) የእግዚአብሔርን ኃይል በፈለግህ ጊዜ ምን ተከሰተ?

13ኛ ጥያቄ፦ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙትን ዐበይት መንፈሳዊ ትምህርቶች ዘርዝር።

ሁለተኛ ቀን ኢሳይያስ 41

14ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ሌላው ሰው ሲናገር ተፈጽሞ ያየኸው ትልቅ ትንቢት ምን ነበር? ለ) ትንቢቱ በተሰጠበትና በተፈጸመበት ጊዜ መካከል ስንት ዓመታት ተቆጠሩ? ሐ) ስለ ሩቅ ጊዜ የሚነገሩ ትንቢቶች ስለ ቅርብ ጊዜ ከሚነገሩት በላይ አስቸጋሪ የሚሆኑት እንዴት ነው?

በቅርብ ጊዜ ስለሚፈጸም ትንቢት ተናግሮ ተግባራዊ ማድረጉ በአንጻራዊ ሁኔታ ቀላል ነው። ለዚህም ምክንያቱ አንዳንድ ጠቋሚ ነገሮች ስለሚኖሩ ነው። ለምሳሌ፥ ኮሚኒዝም በምሥራቅ አውሮፓ ከወደቀ በኋላ በኢትዮጵያም እንደሚወድቅ መተንበዩ ቀላል ነው። ነገር ግን ከብዙ ዓመታት በኋላ ስለሚፈጸም ነገር መተንበዩ አስቸጋሪ ነበር። በኢሳይያስ 41፡1-45 እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሚገኙት እጅግ አስደናቂ ትንቢቶች አንዱን ለኢሳይያስ ገልጾለታል። ትንቢቱ እጅግ አስደናቂ በመሆኑ በእግዚአብሔር የመተንበይ ችሎታ የማያምኑ ምሑራን ይህ ክፍል ከስተቱ ከተፈጸመ በኋላ እንደ ተጻፈ ያስባሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር የወደፊቱን ክስተት ሊናገር እንደሚችል የምናምን ሰዎች ከዚህ ታላቅ ትንቢት ጋር አንታገልም። እግዚአብሔር ከ170 ዓመታት በፊት ቂሮስ የተባለ ንጉሥ አይሁዶች ከምርኮኛነታቸው ወጥተው ወደ አገራቸው እንዲሄዱ የሚያደርግ መሆኑን ገልጾአል። እነዚህ ትንቢቶች በትክክል በመፈጸማቸው የሚያመልኩት አምላክ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ለአይሁዶች አስገንዝቦአቸዋል።

15ኛ ጥያቄ፦ ኢሳይያስ 41ን አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ደሴቶችና አሕዛብ በፊቱ በፍርድ እንዲሰባሰቡ የጠራቸው ለምንድን ነው? (ቁ. 1፥ 5-6፥ 21-29)። ለ) በቁጥር 2 ላይ ለቀረበው ጥያቄ መልሱ ምንድን ነው? ሐ) እግዚአብሔር ከምሥራቅ ለሚመጣው ምን ዓይነት ኃይልን ይሰጠዋል? (ቁ. 2-4፤ 25-31)። መ) ይህ ምዕራፍ በሰዎች የተሠሩትን ጣዖታት ኃይል-አልባነት የሚያሳየው እንዴት ነው? በወደፊቱም ጉዳይ ላይ ሳይቀር የእግዚአብሔርን ኃይል የሚያሳየው እንዴት ነው? ሠ) እግዚአብሔር ያበረታታቸው ዘንድ ለእስራኤላውያን የሰጣቸውን የተስፋ ቃሎች ዘርዝር። ረ) የዚህን ምዕራፍ ትምህርት በአንድ አንቀጽ ጠቅለል አድርገህ ጻፍ።

በምዕራፍ 41 ኢሳይያስ በተምሳሌታዊ መንገድ ፍርድ ችሎት በቀረቡት ሁለት ወገኖች መካከል የሚካሄድ መወነጃጀል የሚመስል

ነገር ጽፎአል። በአንድ በኩል የምድር አሕዛብና ጣዖቶቻቸው ነበሩ። በሌላ ወገን ደግሞ ፈራጅም ተፎካካሪም የሆነው አምላክ ነበር። የፉክክሩ ዓላማ ማን የበለጠ ኃይል እንዳለው፥ ወደፊት የሚከሰተውን ነገር በመተንበይ ወደ ፍጻሜ እንደሚያመጣና እስራኤላውያንን ሊረዳ እንደሚችል መወሰን ነበር።

1. ለደሴቶች፥ ለአሕዛብና አማልክቶቻቸው የቀረበ ተግዳሮት (ኢሳ. 41፡1–2 አንብብ)

እግዚአብሔር ሉዓላዊና ሁሉን ቻይ ፈጣሪ በመሆኑ ጥሪው የቀረበው በእርሱ በኩል ነበር። የተለያዩ የዓለም አገሮች በፊቱ እንዲቆሙ ጠየቃቸው። እግዚአብሔር በፊቱ እንዲቀርቡ አዘዛቸው እንጂ ወደ እነርሱ ለመሄድ ራሱን ዝቅ አላደረገም። በደሴቶች የተወከሉት አነስተኛና ሩቅ የምድር ነዋሪዎች በፊቱ እንዲቀርቡ ተጠየቁ። ይበልጥ ትላልቅና ኃያላን አገሮች በተምሳሌትነት የተወከሉባቸው አሕዛብም ወደ እርሱ እንዲቀርቡ ተጠየቁ። እግዚአብሔር ደሴቶች በፊቱ ዝም እንዲሉ አዘዛቸው። ከፊቱ ስለቆሙ ማንነታቸውን የሚገልጸው ተግባራቸው እንጂ ንግግራቸው አልነበረም። አሕዛብም በተቻላቸው መጠን እርሱን ይገዳደሩ ዘንድ ያላቸውን ኃይል ሁሉ አስተባብረው እንዲቆሙ ጠርቶአቸዋል። ቀደም ሲል እግዚአብሔር የሕዝቡን ኃይል እንደሚያድስ የተናገረ ሲሆን አሁን እነዚህ ወገኖች ከእርሱ ታላቅ ኃይል ጋር ለመወዳደር ሰብአዊ ኃይላቸውን እንዲያድሱ ይመክራቸዋል። ደሴቶችና አሕዛብ በእግዚአብሔር ፊት ይቀርቡና በሁለት ምድብ ተከፍለው ማን የበለጠ ኃይል እንዳለው ይፈታተናሉ። በዚህ የፍርድ ስፍራ የበለጠ ኃይል ያላቸው የአሕዛብ አማልክት ወይም ዘላለማዊ የእስራኤል አምላክ የሆነው እግዚአብሔር መሆኑ ይለይለታል።

2. የመጀመሪያው ተግዳሮት፥ እግዚአብሔር የዓለምን አገሮች ለማሸነፍ ከምሥራቅ ድል አድራጊን ያስነሣል (ኢሳ. 41፡2–8)

እግዚአብሔር ተግዳሮቱን ይህንን ኃይለኛ መሪ ከምሥራቅ ያስነሣው ማን ነው? በሚል ጥያቄ ይጀምራል። መልሱ «እግዚአብሔር» የሚል ነው። መሪውን ያስነሣው፥ የተቆጣጠረውና የሚያከናውናቸውን ተግባራት የወሰነው እግዚአብሔር ነው። እንዲሁም ደግሞ መሪዎችን ሁሉ የሚያስነሣውና ሊያደርጉ የሚችሉትንና የማይችሉትን የሚወስነው እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ኃይለኛ መሪ የተነገረውን ልብ በል።

ሀ. ከምሥራቅ ይመጣል። (የሜዶንና ፋርስን ካርታ ከመጽሐፉ መጨረሻ ላይ ተመልከት።) ምሥራቅ ሁለት ስፍራዎችን ሊያመለክት

ይችላል። <u>በመጀመሪያ</u>፥ የአይሁዶች አገር ከሆነችው ከፍልስጥኤም በስተ ምሥራቅ ማለት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ብዙውን ጊዜ በሚሰጻጣሚያ ሸለቆ ስለሚገኙት አገሮች በሚናገርበት ጊዜ «ሰሜን» የሚለውን ይጠቀማል። <u>ሁለተኛ</u>፥ ይበልጥ ሊሆን የሚችለው ከባቢሎን በስተ ምሥራቅ ነው። ቀጣይ የዓለም ኃያላን የሆኑት የሜዶን ሰዎች የሚገኙት እዚህ ነበር።

ለ. የተጠራው በጽድቅ ነበር። እግዚአብሔር የተጠራው መሪ ጻድቅ ነው አላለም። ነገር ግን በጽድቅ እንደጠራው ገልጾአል። እግዚአብሔር በባቢሎን ላይ የወሰደው እርምጃ ትክክል ነበር። እግዚአብሔር አይሁዶችን ለመቅጣት በመሣሪያነት የተጠቀመባት ባቢሎን ብዙ አገሮችን ስላወደመች ለቅጣት ደርሳ ነበር። ባቢሎናውያን ትዕቢተኞችም ስለነበሩ እግዚአብሔር በአሦር ላይ እንደወሰደው ዓይነት የቅጣት እርምጃ በእነርሱ ላይ መውሰዱ ትክክል ነበር። የእግዚአብሔር የጽድቅ ዓላማዎች ሕዝቡ ከምርኮኛነት ተላቅቀው ወደ አገራቸው የሚመለሱበትንም ሁኔታ ያካተተ ነበር።

ሐ. ወደ እግዚአብሔር አገልግሎት ተጠራ። (በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱሳችን «ወደ እግሩ የጠራው» ተብሎአል። ይህም ራስን ዝቅ አድርጎ ማገልገልን የሚያመለክት ነው።) ይህ ንጉሥ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆኑን በሚቀጥሉት አራት ምዕራፎች ውስጥ እንመለከታለን። ይህም በማወቅ ያደረገው ሳይሆን ሳያውቅ የእግዚአብሔርን ዓላማዎች የፈጸመበት አገልግሎት ነው።

መ. ኃያል ተዋጊ ነበር። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበር ይህ ሰው ታላላቅ አገሮችንና ነገሥታትን ለማንበርከክ ችሎአል። እነዚህን ወገኖች ለማጥፋት ሰይፍና ቀስትን ተጠቅሞአል። ፋርሳውያን በቀስት ጠላቶቻቸውን ከርቀት በመግደል የታወቁ ነበሩ። እነዚህን አገሮች በሚያወድምበት ጊዜ በዚህ ኃያል ተዋጊ ላይ የሚደርስ ጉዳት አይኖርም። ከዚህ በፊት አይቶአቸው የማያውቃቸውን አገሮች ሁሉ ያሸንፋል። እንደውም የሜዶንና ፋርስ መንግሥት የትንሹ እስያን አካባቢዎች ሁሉ ተቆጣጥሮአል። ይህም እንደ አሦር፥ ባቢሎንና ግብፅ ካሉት ኃያላን አገሮች የትኞቹም ያልፈጸሙት ነው።

በኋላ በኢሳይያስ 45፡1 የዚህ ኃያል ተዋጊ ስም ቂሮስ እንደሚባል ተገልጾአል። ምናልባትም ኢሳይያስ ይህንን ትንቢት ግልጽ ያላደረገው ሆን ብሎ ሊሆን ይችላል። ምንም እንኳ ስለ ቂሮስ ቢያስብም ይህ ሰው እግዚአብሔር በአንድ አገር ላይ እንደሚያነሣው እንደ ማንኛውም ሰው ነበር። አንድን መሪ የሚያስነሣውና ምን እንደሚያደርግ የሚወስነው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ከ170 ዓመታት ቀደም ብሎ ባቢሎንን የሚያሸንፈውን አገርና ንጉሥ ስም

መጥቀሱ አስደናቂ ነገር ነው። ታላቁ ቂሮስ ከ559–530 ዓ.ዓ. ፋርስን የገዛና በ539 ባቢሎንን ያሸነፈ መሪ ነበር።

አሁንም እግዚአብሔር የባቢሎንን ውድቀት ያቀደውና ተግባራዊ ያደረገው ማን ነው? ሲል ይጠይቃል። ይህንን የወሰነው የአጽናፈ ዓለሙ አምላክ የሆነው እግዚአብሔር ራሱ ነበር። ከመፈጸሙ ከአራት ትውልዶች በፊት እግዚአብሔር ሊሆን የሚገባውን ነገር ወስኖአል። የእግዚአብሔር ዕቅዶች ከዘላለም ዘመናት በፊት የተወሰኑ በመሆናቸው ቂሮስ ባቢሎንን ለመደምሰስ የእግዚአብሔርንም ሕዝብ ከምርኮ ለመልቀቅ መምጣቱ የማይቀር ነው። የሥራው ጀማሪና ፈጻሚ እግዚአብሔር ነው። ሕዝቡ ከምርኮ ይወጣ ዘንድ ቂሮስን ተጠቅሞ በአገሮች ላይ ፍርድን ማምጣት የጀመረው እግዚአብሔር ነበር። ለቂሮስም ይሁን በቂሮስ አማካኝነት ሥራውን የሚያከናውነው እግዚአብሔር ነበር።

ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚገልጽ ሌላ ስያሜ አቅርቦአል። እግዚአብሔር የመጀመሪያና የመጨረሻው ነው። ሁሉም ነገር ሲጀመር እግዚአብሔር በዚያ ነበር። ሁሉም ነገር ከመኖር ወዲያ ሲርቅም እግዚአብሔር በስፍራው ይኖራል። እርሱ ከየትኛውም አገር በፊት የነበረ ሲሆን አገሮች ሁሉ በሚሸነፉበት ጊዜም ስፍራውን አይለቅም። ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻ ድረስ ጌታ ነው። እስከ መጨረሻው ሳይለወጥ ታሪክን ሁሉ በፍጹማዊ ሉዓላዊነት የሚቆጣጠረው እርሱ ነው። ይኸው ስያሜ ለኢየሱስ ክርስቶስ በመሰጠቱ ራሱን «የመጀመሪያውና የመጨረሻው» ሲል ይጠራዋል (ራእ. 1፡8፥ 17፤ 2፡8)።

16ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ለክርስቲያኖች ታሪክን የሚቆጣጠረው እግዚአብሔር እንጂ የዓለም መሪዎች አለመሆናቸውን መገንዘቡ ለምን ይጠቅማል? ለ) ከቅርብ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር አገሪቱን በመቆጣጠር ላይ እንደሆነ የሚያሳዩትን አንዳንድ ክስተቶች ዘርዝር። ሐ) ይህ ስለ ወደፊቱ ምን ተስፋ ይሰጠናል?

ለመሆኑ ሰዎች የታመኑባቸው ደሴቶች፥ አሕዛብና ጣዖታት የሰጡት ምላሽ ምን ነበር? ከፍተኛ ፍርሃትና ዝለት በመኖሩ እርስ በርሳቸው ተረዳድተው ለመቆም ሞከሩ። ጠንክረው ለመቆም እርስ በርሳቸው ለመበረታታት ጣሩ። ቂሮስን ፈርተውት ነበር? አዎን! ከዚያ በላይ ደግሞ እንደ ኃያል ተዋጊ ሆኖ የሚመጣውን እግዚአብሔርን ፈርተውት ነበር። በመጠኑም ቢሆን ከሕያው አምላክ ይታደጉናል በሚል እምነት አሕዛብ ወደ ሌሎች አማልክት ተጠጉ። አሕዛብ አንድ ሰው ብዙ አማልክትን የሚያመልክ ከሆነ ከእነዚህ መካከል አንዱ የመርዳት ብቃት ስለሚኖረው የተሻለ የጥበቃ ዋስትና እንዳለው የሚያምኑ መሆናቸውን ከዚህ እንረዳለን። በሕንድ ወደ ሦስት

ሚሊዮን አማልክት የሚመለኩት አንድ ችግር የተነሣ እንደሆነ አማልክቱ የመፍትሔ ጭራ ያስጨብጡናል በሚል እምነት ነው። የሚገርመው ግን አሕዛብ የእግዚአብሔርን ኃይል ካዩ በኋላም ወደ እውነተኛው አምላክ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው አለመቅረባቸውና ይቅርታ አለመጠየቃቸው ነው።

አሁንም ኢሳይያስ አንድ ሰው ጣዖትን በሚሠራበት ጊዜ ምን እንደሚከሰትና አምልኮተ ጣዖት ምን ያህል የሞኝነት ተግባር እንደሆነ ገልጾአል። እንጨቱን የሚጠርበው አናጺ ወርቅ አቅላጩን ያጽናናዋል። በጣዖት ቀረጻው ተግባር ላይ የተሰማሩ ሰዎች ሁሉ ጣዖቱ የሕያው አምላክን ያህል ኃይል እንደሚኖረው በመግለጽ እርስ በርሳቸው ይጽናናሉ። በመጨረሻም ጣዖቱ እንዳይወድቅ በችንካር ያጣብቁታል።

የበለጠ ኃይል ያለው የትኛው አምላክ ነው? አንዱ ያልተፈጠረና ዘላለማዊ ዕቅዶች ያሉት ሲሆን፥ ሌላኛው በሰው ልጆች የተሠራ ነው። እንዳይወድቅ በምስማር የተቸነከረም ነው። በግልጽ እንደሚታየው፥ ሊከበርና ሊፈራ የሚገባው ሕያው፥ የማይታየውና ዘላለማዊው አምላክ ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር በመጀመሪያ ተግዳሮት አሸናፊነቱን አረጋግጦአል።

3. እግዚአብሔር ባሪያውን እስራኤልን እንደሚንከባከብ ቃል ገባ (ኢሳ. 41፡18–20)

ሀ. አይሁዶች አሁንም የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ ነበሩ (ኢሳ. 41፡8–10 አንብብ)

ኢሳይያስ በመቀጠል ሁለተኛውንም የእግዚአብሔርን አገልጋይ ገልጾአል። የመጀመሪያው አገልጋይ ተዋጊው ቂሮስ ሲሆን፥ ሁለተኛው ምርጥ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆነው እስራኤል ነው። አሕዛብ በቂሮስ በኩል፥ ከመጣው ከእግዚአብሔር ቁጣ ለመዳን ወደ ጣዖታት ፊታቸውን መለሱ። አይሁዶችስ ምን ያድርጉ? ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸውን ታሪካዊ ዝምድና ለማሳየት ኢሳይያስ የአይሁዶች አባት የሆነውን አብርሃምን ጠቀሰ። አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ ነበር። ልክ እንደ አብርሃም ማንኛውም አይሁዳዊ የእግዚአብሔር ወዳጅ ሊሆን ይችል ነበር። ኢሳይያስ አብርሃምን የጠቀሰው እግዚአብሔር ለአይሁዶች ፍቅሩንና ጥበቃውን ለማሳየት እንደ መሠረት የተጠቀመበትን ቃል ኪዳን ለማስገንዘብ መሆኑ አይጠረጠርም።

አይሁዶች እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን የተሰረዘ ሳይመስላቸው አልቀረም። ከአገራቸውና ከቤተ መቅደሳቸው ርቀው በአሕዛብ መካከል ተበትነው ነበር። ኃጢአታቸው የወደፊት ሕይወታቸውን አጨልሞባቸው ይሆን? እግዚአብሔር «አይደለም!»

ሲል ተናገረ። አሁንም የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ ነበሩ። እግዚአብሔር በአንድ ወቅት አብርሃምን ወደ ተስፋዪቱ ምድር እንደጠራ ሁሉ አይሁዶችን ከምድር ዳርቻ ይሰበስባቸዋል። ከዓለም አሕዛብ ሁሉ እግዚአብሔር መርጦአቸዋል። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ላለመታዘዛቸው ቢፈርድባቸውም ይህ ሙሉ ለሙሉ እንደሚጣሉ አያመለክትም። እግዚአብሔር አሁንም የእስራኤል አምላክ ነበር። ስለሆነም እስራኤላውያን የሚፈሩት ነገር አልነበራቸውም። በችግሮቻቸው ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር አሁንም አምላካቸው እንደሆነና እንደማይተዋቸው ማስታወስ ነበረባቸው። በጽልመታም የምርኮ ዘመናቸውና ወደ አገራቸው ለመመለስ ረዥሙን ጉዞ ሲያያዙት እግዚአብሔር አብሮአቸው ሊሆን ቃል ገባ። ሊረዳቸውና ሊያበረታታቸው ቃል ገባ። ሕጻን ልጅ በሸካራ መንገድ ላይ እየሄደ ሳለ እንዳይወድቅ አባቱ እጁን እንደሚይዝ ሁሉ እግዚአብሔርም በምርኮና በብሔራዊ ውጥረት ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ እጃቸውን ይይዛል። አንድ ቀን የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነችው እስራኤል እንደ ካህናት መንግሥት በመሥራት የእግዚአብሔርን ክብር ለማወጅ የተመረጠችበትን ጥሪ ተግባራዊ ታደርጋለች።

ለ. እግዚአብሔር የእስራኤላውያንን ጠላቶች ያጠፋል (ኢሳ. 41፡11–16 አንብብ)

የታላላቅ ጠላቶቻቸውስ ጉዳይ? በምርኮኛነት የያዘቻቸው ታላቋ ባቢሎንስ? አይሁዶች በአዳኝ ወጥመድ እንደተያዘች ወፍ የተስፋ ቢስነት ስሜት ተጫናቸው። እግዚአብሔር ግን አንድ ቀን ጠላቶቻቸው ፈጽመው እንደሚጠፉ ለአይሁዶች የተስፋ ቃል ገብቶላቸው ነበር። እግዚአብሔር ስለሚያሸንፋቸው ምልክታቸው አይገኝም። ጠላቶቻቸው ከእነርሱ ጋር በሚዋጉበት ጊዜ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ይቆማል። የፈጣሪ አምላክን አገልጋይ የሚነካ ሰው ወይም አገር ኃያል ተዋጊ ከሆነው ጌታ ጋር ይጋጫል።

እግዚአብሔር አይሁዶችን «ያዕቆብ» ሲል የአያት ቅድማያታቸው ስም በሆነው መጠሪያ ይገልጻቸዋል። የስሙ ፍች «አታላይ» ማለት ሲሆን፥ በዚህ ስፍራ አይሁዶች እግዚአብሔርን ከመጠበቅ ይልቅ በራሱ መንገድ ነገሮችን ከእጁ ለማስገባት ይፈልግ የነበረውን አባታቸውን እንዴት እንደሚመስሉ ለማመልከት እንዳገለገለ አያጠራጥርም። በታሪክ ሲታይ፥ አይሁዶች ከእግዚአብሔር ይልቅ በራሳቸው ላይ ይደገፉ ነበር። እንዲሁም ደግሞ እግዚአብሔር ያዕቆብን ከሜሶጶጣሚያ ወደ ተስፋዪቱ አገር እንዲሄድ የተናገረበትንም ሁኔታ ለማመልከት ያገለገል ሊሆን ይችላል (ዘፍጥ. 31፡13)። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የያዕቆብ ትውልዶች ሜሶጶጣሚያን ትተው ወደ ተስፋዪቱ አገር እንዲሄዱ እየተናገራቸው ነበር። ከዓለም ታላላቅ

አገሮች ጋር ሲነጻጸር ያዕቆብ ወይም እስራኤል «ትል» መሆኑ እውነት ነው። (እግዚአብሔር ለወሰነውና ሌሎች ለናቁት ሥራ ብቁ አልነበረም።) ነገር ግን የሚቤዣቸው (ከምርኮ ነፃ የሚያወጣቸው) አምላክና የእስራኤል ቅዱስ (ከአማልክት ሁሉ የላቀውና ከእስራኤል ጋር ልዩ ግንኙነት ያለው እግዚአብሔር) ከጠላቶቻቸው ነፃ ያወጣቸዋል። (ማስታወሻ፡ በዚህ ስፍራ ስለ መቤዠት የሚናገረው ቃል በብሉይ ኪዳን በባሪያነት የተያዘን ሰው ዘመዱ የግድ ገንዘብ ከፍሎ እንደሚቤዥ የሚገልጸው ቃል ነው። ይህም የቅርብ ዘመድ መቤዠት የሚባል ነው (ዘሌዋ. 25፡24-25)። እግዚአብሔርም የአይሁዶች አባት እንደ መሆኑ ቤተሰቡን በመጠበቅ ከባርነት ይመልሳቸዋል።)

አንድ ቀን ደካማይቱ እስራኤል ወደ ኃያልነት ትለወጣለች። ትሉ እንደ አዲስ ባለ ጥርስ ማሄጃ በመሆን እህሉን እያበጠረ ፍሬውን ከገለባው ይለያል። ኃያላን የዓለም አገሮችና የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚጋፈጡአቸው እንደ ታላላቅ ተራሮች የመሳሰሉ ነገሮች፥ ብሎም የሕዝበ-እግዚአብሔር መሰናክሎች የሆኑ ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ሕዝብ ፊት ይከስማሉ። የማበጠር ተግባር በሚካሄድበት ወቅት እንደሚበን እብቅ እንዲሁ ዳግም ላይመለሱ ይወገዳሉ። ለዚህም ምክንያቱ የእስራኤል ጥንካሬ ሳይሆን የእግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር መሆን ነው። ይህ ታላቅ ድል የእግዚአብሔር ክብር በሕዝቡ ላይ እንደተቀመጠ የሚያመለክት ነበር። ሕዝቡም ለስሙ የሚገባን ክብር በመስጠት እግዚአብሔርን ያከብሩታል።

ይህ ትንቢት ሙሉ ለሙሉ የሚፈጸምበትን ጊዜ ማወቁ አስቸጋሪ ነው። አይሁዶች ከባቢሎን ምርኮ በተመለሱ ጊዜ እግዚአብሔር ባደረገላቸው ጥበቃ ውስጥ በከፊል ተፈጻሚ ሆኗል። ነገር ግን ከምርኮ ከተመለሱ በኋላ ሙሉ ለሙሉ አልተፈጸመም። በታሪካቸው ሁሉ ብዙውን ጊዜ አይሁዶች የኖሩት በአሕዛብ አገዛዝ ሥር ነው። ምናልባትም ትንቢቱ ሙሉ ለሙሉ የሚፈጸመው መሢሑ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ በአይሁድና በዓለም ላይ ሁሉ በሚገዛበት ወቅት ይሆናል።

ሐ. እግዚአብሔር በበረሃ ውስጥ ይመራቸዋል (ኢሳ. 41፡17-20 አንብብ)

አይሁዶች ለመመለስ የተጠቀሙበት ከባቢሎን ወደ ይሁዳ የሚወስደው መንገድ 800 ኪሎ ሜትር ያህል ነበር። ዕቃዎቻቸውንና ትናንሽ ልጆቻቸውን ተሸክመው የሚሄዱት አይሁዶች በዚህ ረዥም መንገድ ለብዙ ወራት ለመጓዝ ይገደዱ ነበር። መንገዱም ደግሞ አስቸጋሪ ነበር። ኢሳይያስ መንገዱ በተለይም ብዙም ገንዘብ ለሌላቸውና ረዥም መንገድ ለመሄድ ላልተዘጋጁት አይሁድ ምን

እንደሚመስል ገልጾአል። ውኃ ስለማይገኝ ሞት ያሰጋቸዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር በመጀመሪያው የዘጸአት ወቅት በሙሴ ለተመሩት እስራኤላውያን በተአምራዊ መንገድ ውኃን እንዳፈለቀላቸው እንዲሁ ለሁለተኛው ዘጸአት ውኃን ያዘጋጅላቸዋል። በወናዎቹ ኮረብታዎች ላይ ወንዞችን ያደርጋል። ውኃ የሚገኘው ከሸለቆዎች እንጂ ከኮረብታዎች ባለመሆኑ ይህ እግዚአብሔር የማይቻለውን ነገር እንደሚያደርግ ያሳያል። እግዚአብሔር የውኃ ፍላጎታቸውን እንደሚያሟላላቸው እንዳረጋገጠ ሁሉ ወደ አገራቸው በሰላም ለመድረስ የሚያስፈልጓቸውን የምግብና የማናቸውም ነገሮች ፍላጎታቸውንም ያሟላላቸዋል።

እግዚአብሔር በሚሄዱበት በረሃማ መንገድም ነገሮችን ይለዋውጣል። ዝግባው፥ ግራሩ፥ ባርሰነቱ፥ የዘይቱን ዛፍ፥ ጥዱ፥ አስታው፥ ወይራውም እንዲያብቡ ያደርጋል። በተለይም እንደ ዝግባና ጥድ ዓይነቶቹ ውኃ የሚፈልጉ ዛፎች በመሆናቸው በበረሃማ ስፍራ የሚበቅሉ አይደሉም።

እነዚህ ትንቢቶች ለአይሁዶች የተሰጡት ከምርኮ ወደ ይሁዳ በሚመለሱበት ጊዜ እግዚአብሔር አብሮአቸው እንደሚሆንና የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ እንደሚያሟላላቸው ለማረጋገጥ ነው። ለሕዝበ-እስራኤል ወደ አገር ቤት የመመለሱን ሂደት ጣፋጭ ያደርግላቸዋል። ነገር ግን እግዚአብሔር ምንም ዓይነት አዳዲስ ወንዞችን ወይም ዛፎችን በምድረ በዳ እንዳላበጀ ግልጽ ነው። ኢሳይያስ የተመለከተው በዘሩባቤል መሪነት እስራኤላውያን ከምርኮ መመለሳቸውን ሳይሆን፥ እግዚአብሔር ምድረ በዳውን የሚለውጥበትን የመጨረሻውን ዘመን ይመስላል (ኢሳ. 32ን ተመልከት)። ይህ የአይሁዶች ከምርኮ መመለስ እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን ለሕዝቡ የሚያቀርባቸውን በረከቶች ያመለክታል። ኢሳይያስ በሕዝቡ ምድራዊ የምናኔ ጉዞ ወቅት እግዚአብሔር አብሮአቸው እንደሚሆን የሚያሳይ ተምሳሌታዊ ምስል እየሠራ ሊሆን ይችላል። የውኃ ምንጮች፥ ወንዞችና ጥላው በምናኔ ጉዞው ወቅት የሚመጡትን የእግዚአብሔር መንፈሳዊና አካላዊ በረከቶች ያመለክታሉ።

የመጨረሻው ውጤት ግልጽ ይሆናል። እንደ መጀመሪያው የግብፅ ዘጸአት (ኢያ. 2፡8-10)፥ ሁለተኛውም ዘጸአት የእግዚአብሔር ሥራ እንደሆነ ሁሉም ይገነዘባል። ከስተቱ ከመፈጸሙ ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ዐቅዶታል። እግዚአብሔር የራሱን ልጆች የሚንከባከብ ተአምር-ሠሪና ሕያው አምላክ በመሆኑ ለልጆቹ ሲል ተአምራት መሥራቱ እሙን ነው። ከዚያ በኋላ ዓለም ሁሉ የእግዚአብሔርን ማንነት ይገነዘባል። እግዚአብሔር ታላቅ ፈጣሪ አምላክ፥ የሕዝቡ ጠባቂና ኃያል እንደሆነ ይረዳሉ። እግዚአብሔር

ሕዝቡን በሚባርክበት ጊዜ የሚገደው የሕዝቡ እርሱን ማምለክ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ያንኑ ተመልክተው ማምለካቸው ነው። በእኛ አማካኝነት ሌሎችን ይባርክ ዘንድ እኛን ይባርካል [መዝ. (67)፡1–2፤ 6–7]።

17ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር እኛን የሚባርክበት ዋነኛው ምክንያት ጥሩ ሕይወት እንድንኖር ነው ብለው የሚያስቡት እንዴት ነው? ለ) እግዚአብሔር እኛን የሚባርከን ለሌሎች በረከት እንድንሆን ነው ብሎ ማሰቡ በአመለካከታችን ላይ የሚያስከትለው ለውጥ ምንድን ነው?

4. ሁለተኛው ተግዳሮት–የአሕዛብ ጣዖታት የወደፊትን ክስተቶች በመተንበይ ኃይላቸውን ማሳየት ነበረባቸው (ኢሳ. 41፡21–29)

ሀ. እግዚአብሔር የአሕዛብ ጣዖታት የወደፊት ክስተቶችን እንዲተነብዩ ይጠይቃቸዋል (ኢሳ. 41፡21–24 አንብብ)

ከአማልክት ጣዖታትና ሕያው ፈጣሪ ከሆነው እግዚአብሔር ኃይለኛው ማን ነው? አይሁዶች በተለይም በምርኮ ምድር በጣዖታት ዙሪያቸውን ታጥረው በተቀመጡበት ወቅት ሊያስቡበት የሚገባው ይህንኑ ነበር። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፥ ኢሳይያስ 41 በሕያው አምላክና ሰዎች በሠሯቸው ጣዖታት መካከል የሚካሄድ ተግዳሮት አካል ነው። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ጣዖታቱ ስለ ወደፊት ለመተንበይ መቻላቸውን በመጠየቅ ተገዳድሯል። ተግዳሮቱ ይካሄድ ዘንድ ጣዖት አምላኪዎቹ ጣዖቶቻቸውን ይዘው ወደ ፍርድ ችሎት እንዲቀርቡ ይጋብዛቸዋል። (የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ‹ያምጡ› ብቻ ነው የሚለው። ይህም ጣዖቶቻቸውን ለማለት ነው።) እግዚአብሔር ቀደም ሲል ወደፊት የሚፈጸሙትን ክስተቶች አስመልክቶ ትንቢታዊ መልእክት ያስተላለፈ ሲሆን፥ ከእነዚህም መካከል ቂሮስ አይሁዶችን ከምርኮ የሚያስለቅቅ መሆኑ ተገልጾአል። ጣዖታቱ በተመሳሳይ መንገድ ስለ ወደፊት ሊተነብዩ ይችሉ ይሆን? ጣዖታቱ እውነተኞች ከሆኑ ሰዎች ሁሉ ኃይላቸውን ያውቁ ዘንድ የወደፊቱን ማሳወቅ መቻል ነበረባቸው። የሩቁን መተንበይ በጣም የሚከብዳቸው ከሆነ የቅርቡን እንዲተነብዩ በመጠየቅ እግዚአብሔር ተገዳደራቸው። ወይም ደግሞ የወደፊቱን መተንበይ ካቃታቸው ኃይላቸውን ለማሳየት የፈለጉትን ነገር እንዲያደርጉ ጠየቃቸው። ይህም የሞተን ሰው እንደ ማስነሣት ዓይነት መልካም ተግባር ወይም እንደ ሰዶም ዓይነቷን ከተማ እንደ ማጥፋት ዓይነት መጥፎ ተግባር ሊሆን ይችላል። እውነተኛ አማልክት ከሆኑ፥ በከፍተኛ ኃይል በመሥራት በሰዎች ልብ ውስጥ ፍርሃትን የመጫር ብቃት ይኖራቸው ነበር።

ተግዳሮቱ የቀረበላቸው ጣዖታት ግን መጪውን ጊዜ መተንበይ አልቻሉምና ዝምታ ዋጣቸው። መልካምም ሆነ ክፉ ተአምራታዊ ተግባር ሊያከናውኑ አልቻሉም ነበር። ስለሆነም እግዚአብሔር እነዚህ አማልክት ጥቅምም ሆነ ኃይል የሌላቸው ሕይወት-አልባ የእንጨትና የወርቅ ጥርቅም መሆናቸውን ገልጾአል። በሙሉ ኃይሉ በሕያው አምላክ ሳያምን ቀርቶ በሰው ልጆች በተሠራ ነገር የሚታመን ማንም ቢሆን አስጸያፊ ነው። እነዚህ ጣዖታት የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚያስከትል ተግባር የሚፈጽሙ ከፉዎች ናቸው።

18ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ይኸው ተመሳሳይ ተግዳሮት ዛሬ ለጠንቋዮች የሚሠራው እንዴት ነው? ለ) ይህ ምንባብ ክርስቲያኖች ለችግሮቻቸው መፍትሔ ለማግኘት መናፍስት ጠሪዎችን፥ ጠንቋዮችንና ምትሐተኞችን እንዳይጠቀሙ የሚያስተምረው እንዴት ነው? ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች ለችግሮቻቸው በእግዚአብሔር ከመታመን ይልቅ ወደ ምትሐት ወይም ጥንቆላ የሚያዘነብሉት ለምንድን ነው? መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንን ፈተና ለማስወገድ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? ሠ) ይህንን ፈተና ለመቋቋም የእግዚአብሔርን ባሕርይ በግልጽ መረዳት የሚያስፈልገው እንዴት ነው?

ለ. እግዚአብሔር የሕዝቡ ነፃ አውጭ ከሰሜን እንደሚመጣ በመተንበይ ችሎታውን አሳየ (ኢሳ. 41፡25-29)።

ምንም እንኳ ጣዖታት ምንም ነገር ለመተንበይ ባይችሉም እግዚአብሔር የፋርስ ንጉሥ የሆነው ባሪያው ቂሮስ እንደሚመጣ ተናግሮአል። ቀደም ሲል ይህ ነፃ አውጭ ከምሥራቅ ይመጣል ያለ ሲሆን አሁን የቂሮስን የድል ፈለግ ይገልጻል። ይህ ሰው ከሰሜን በደቡብ በኩል ወደነበረችው የአይሁዶች አገር ይጓዛል። ከኢሳይያስ እይታ አንጻር፥ ሜሶጶጣሚያና በተለይም ፋርስ የሚገኙት በሩቅ ሰሜን ነበር።

ኢሳይያስ ይህ ነፃ አውጭ የእግዚአብሔርን ስም እንደሚጠራ ተናግሮአል። ይህ ማለት ቂሮስ እግዚአብሔርን አመነ ማለት ይሆን? አይደለም። በኢሳይያስ 45፡4-5 ቂሮስ ኃይሉን ያገኘው ከእግዚአብሔር ዘንድ መሆኑን እንደማያውቅ ተገልጾአል። ነገር ግን ቂሮስ የአማልክቱን መኖር እንደሚቀበል ሁሉ እግዚአብሔር እንዳለ ያውቃል። ስሙንም ይጠራል። ስለሆነም አይሁዶች ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ትእዛዝ ባወጣበት ወቅት የእግዚአብሔርን ስም በአዋጁ ውስጥ አካትቶአል (ዕዝራ 1፡2 ተመልከት)። ቂሮስ ከእርሱ በፊት እንደነበሩት አሦራውያንና ባቢሎናውያን ሳያውቅ የእግዚአብሔርን ዓላማዎች የሚፈጽም መሣሪያ ነበር። አሦርና ባቢሎን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ፍርድ ለማምጣት ሲያገለግሉ፥ ቂሮስ እና ፋርስ ግን የእግዚአብሔርን ፍርድ ከምርኮኝነታቸው ነፃ ለማውጣት አገልግለዋል። በመጀመሪያው ዘጸአት እግዚአብሔር ሕዝቡን ነፃ ለማውጣት ሙሴን

ከተጠቀመበት ሁኔታ በሚቃረን መልኩ በሁለተኛው ዘጸአት ቂሮስን ተጠቅሞአል።

ቂሮስ ከመወለዱ ከ170 ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ለሕዝቡና ለዓለም የሚሆነውን ነገር አሳውቆአል። በኢሳይያስ 45፡1 ወደፊት የሚመጣውን የነፃ አውጭ ስም ጠቅሶአል። ይህ እግዚአብሔር ሕያው አምላክ እንደሆነና መጽሐፍ ቅዱስም የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ ለማሳየት በዐቢይ መረጃነት የሚያገለግል ከስተት ነው። 170 ዓመታት ወደፊት አሻግሮ የሚመለከትና የሚከሰተውን ነገር የሚገልጸው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እንዲያውም እግዚአብሔር ለቂሮስ ያቀዳቸው ተግባራት ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ የተወሰኑ መሆናቸውን ተናግሮአል። የትኛውም ሰው ወይም ጣዖት ይህንን ከስተት አስቀድሞ ሊገልጥ አልቻለም። ሊገልጥ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነበርና በኢየሩሳሌም ለነበሩት ሕዝቡ ከፍጻሜው 170 ዓመታት ቀደም ብሎ ገልጦላቸዋል።

እንግዲህ ከዚህ የእግዚአብሔርና የጣዖታት ተግዳሮት ሊወሰድ የሚገባው ድምዳሜ ምንድን ነው? ጣዖታት አፍ ስለሌላቸው ራሳቸውን ሊከላከሉ አልቻሉም። ለተከተሏቸው የዓለም መሪዎች ምክር ሊሰጡ አልቻሉም ነበር። ሁሉም ሐሰተኛ አማልክት ነበሩ! ምንም ሊሠሩ አልቻሉም። ለተከተሏቸው ሰዎች ከነፍስ (የውሸት ከንቱ ተስፋዎች) ፥ ከግራ መገባት እና ከጥፋት በቀር የሰጡት ነገር አልነበረም።

19ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በኢትዮጵያ ሰዎች ይረዱናል በሚል እምነት የሚጠጉዋቸውን አንዳንድ ጣዖታት (ሰዎች በእጆቻቸው የሚቀርጹዋቸው ጣዖታት፥ በሰው የተፈጠሩ ትምህርቶች ወይም በመከራ ጊዜ ይረዱናል ብለው የሚታመኑባቸው ነገሮች) ዘርዝር። ለ) ከማይታየው ሕያው ፈጣሪ አምላክ ጋር ሲነጻጸር በእነዚህ ጣዖታት መታመኑ ትርጉም–የለሽ የሚሆነው ለምንድን ነው? ሐ) ስለ እግዚአብሔር ኃይልና በእርሱ ላይ ብቻ ስለ መታመን አስፈላጊነት ከዚህ ምዕራፍ ምን እንማራለን?

ሦስተኛ ቀን — ኢሳይያስ 42

እግዚአብሔር በዚህች ቤተ ክርስቲያን በሚገባ ተጠቅሞአል። በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች በዚህች ቤተ ክርስቲያን አማካኝነት የወንጌሉን ቃል ሰምተዋል። ብዙዎች ደግሞ በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት አምነዋል። አንድ ቀን ግን ቤተ ክርስቲያኒቱ ትበጣበጥ ያዘች። ቀደም ሲል ለቤተ ክርስቲያኒቱ ዕድገት በጋራ የሠሩ ሁለት መሪዎች ነበሩ። አሁን ግን ይባሉ ጀመር። ሰዎቹ ከተለያዩ ጎሳዎች የመጡ ነበሩ። በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ እያንዳንዱ ብዙ ተከታዮች ነበሩት። አንደኛው የሽማግሌዎች ሰብሳቢ እንዲሆን ሲመረጥ የሌላ ጎሳ

አባል የሆኑትን ሰዎች ሁሉ በራሱ ወገኖች ይተካ ጀመር። ስጦታ እንደሌለውና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለማገልገል እንደማይፈልግ ሁሉም ሰው እያወቀ ልጁ ወደ ሥነ መለኮት ኮሌጅ እንዲገባ አስመረጠው። ሌላኛው መሪ ዘመዶቹን፥ ጓደኞቹንና የጎሳውን አባላት ሰብስቦ ክስ ለመመሥረት ተነሣ። ወዲያውም በሰዎቹ መካከል የነበረው ብጥብጥ ታወቀ። ሰዎች ከፕሮግራም ይቀሩ፥ ያችን ቤተ ክርስቲያን ትተውም ወደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ይሄዱ ጀመር። የመንግሥት ሠራተኞችም «ክርስትና እንዲህ ከሆነ ሙስሊም ብሆን ይሻለኛል» ይሉ ጀመር።

20ኛ ጥያቄ፦ ሀ) እነዚህ ሁለት መሪዎች የቤተ ክርስቲያንን መሪነት ምንነት ያላወቁት እንዴት ነው? ለ) የቤተ ክርስቲያናቸውንና የኢየሱስ ክርስቶስን ስም ያጎደፉ ምን ምን የባሕርይ ችግሮች ነበሩባቸው? ሐ) የቤተ ክርስቲያንን ክፍፍል የሚፈጥሩ ሌሎች የመሪዎች ችግሮች ምን ምንድን ናቸው? መ) ፍጹምነትን የተላበሰ የቤተ ክርስቲያን መሪ ምን ምን ባሕርያት ይኖሩታል? ምን ይመስላል? ምን ምን ተግባራትን ያከናውናል?

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ችግሮች የሚታዩት ከመሪዎች መንጭተው በመውጣት ነው። መሪዎቹ ችግሮቹን የሚያመጡት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሪነት የሚያስተምረውን ስለሚዘነጉ ነው። ዛሬ ቤተ ክርስቲያን በከፍፍል የምትታመሰው መሪዎቹ ኢየሱስ ክርስቶስን ሳይሆን ዓለምን ለመሪነት ሞዴል አድርገው ስለሚከተሉ ነው። ይህ ደግሞ አዲስ ችግር አይደለም። እንዲያውም ይህ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሁልጊዜም ሲያሠቃይ የኖረ ችግር ነው። ቀደም ሲል የእስራኤል መሪዎች በአብዛኛው ጠጭዎችና እንደ መበለቶችና እጓለማውታን የመሳሰሉትን ድሆች የሚጨቁኑ እንደነበሩ ከትንቢተ ኢሳይያስ አጥንተናል። ለተቀረው ዓለም የካህናት መንግሥት እንድትሆን የተመረጠችው እስራኤል (ዘጸ. 19፡6) እግዚአብሔርን በአሕዛብ መካከል ወደሚያሳፍር መሣሪያነት ተቀየረች (ሕዝ. 36፡16–23)። የእግዚአብሔር አገልጋይ እንድትሆን የታሰበችው እስራኤል እግዚአብሔርን ትቃወም ጀመር።

ነገር ግን አንድ ቀን ፍጽምናን የተላበሰ አገልጋይ ይነሣና ለመሪዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንዴት መምራት እንዳለባቸው ያሳያቸዋል። ሌላዋ የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሆነችው ከእስራኤል እግዚአብሔር የሚጠብቀውን ነገር ያሟላል። በሚቀጥሉት ሁለት ምዕራፎች ኢሳይያስ ስለዚሁ የእግዚአብሔር አገልጋይ ስለሆነው መሢሕ የገለጸውን አሳብ እናገኛለን። ስለሚመጣው የእግዚአብሔር አገልጋይ የሚናገሩትን እነዚህን ምንባቦች ምሑራን «የአገልጋይ መዝሙሮች» ሲሉ ይጠራሉ። እነዚህ የአገልጋይ መዝሙሮች በኢሳይያስ 42፡1–7፤ 49፡1–6፤ 50፡4–9፤ 52፡13–53፡12 ቀርበዋል።

(ማስታወሻ፡ ምሑራን የአገልጋይ መዝሙሮች በሚያበቁባቸው ስፍራዎች ላይ ባይስማሙም ሁሉም እነዚህ ምንባቦች በአገልጋይ መዝሙሮች ውስጥ እንደሚካተቱ ይስማማሉ።)

በዚህ የትንቢተ ኢሳይያስ ክፍል ለያይተን ልንመለከታቸው የሚገቡ ሦስት አገልጋዮች አሉ። <u>በመጀመሪያ</u>፥ እግዚአብሔር አይሁዶችን ከምርኮ እንዲያስለቅቅ የመረጠው ቂሮስ አለ። <u>ሁለተኛ</u>፥ ለዓለም የእግዚአብሔር አገልጋይ ትሆን ዘንድ የተመረጠችና በታሪክ ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት ያልቻለች እስራኤል አለች። ወደፊት እስራኤል አንድ ቀን እግዚአብሔር የሚጠቀምባት ትሆናለች። <u>ሦስተኛ</u>፥ በእርሱ በኩልና በእርሱ አማካኝነት እግዚአብሔር ለዓለም የወጠናቸው ዕቅዶች ሁሉ ተግባራዊ የሚሆኑበት የእግዚአብሔር ፍጹም አገልጋይ የሆነው መሢሕ አለ። እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

21ኛ ጥያቄ፡– ኢሳ. 42፡1–25 አንብብ። (ሀ) የእግዚአብሔር ባሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያመለክቱትን ባሕርያት ዘርዝር። (ለ) የእግዚአብሔር ባሪያ ከሌሎች ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያመለክቱትን ባሕርያት ዘርዝር። (ሐ) የእግዚአብሔርን ባሪያ ውስጣዊ ማንነት የሚያመለክቱትን ባሕርያት ዘርዝር። (መ) እግዚአብሔር ይህንን ባሪያ የመረጠው ለምን ዓላማ ነው? (ሠ) ይህ ባሪያ ማን ነው? ማቴዎስ 12፡18–21 ተመልከት። (ረ) በኢሳይያስ 42፡10–17 በሚገኘው መዝሙር ውስጥ እግዚአብሔር የተገለጸው እንዴት ነው? (ሰ) እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዲያመሰግኑት የሚያደርግ ምን ተግባር ያከናውናል? (ሸ) በኢሳይያስ 42፡18–25 እስራኤል የተገለጸችው እንዴት ነው? (ቀ) የዚህን ምዕራፍ ዐበይት ትምህርቶች በአንድ አንቀጽ ጠቅለል አድርገህ ጻፍ።

1. መጭው የጌታ ባሪያ (ኢሳ. 42፡1–9)

ሀ. የባሪያው ባሕርይ (ኢሳይያስ 42፡1–4 አንብብ)

በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ስለሚመጣው ባሪያው ገለጻ አድርጓል። ምንም እንኳ ኢሳይያስ የዚህን ባሪያ ማንነት እገሌ ነው ብሎ ባይነግረንም፥ በኋላ ከተሰጡት መግለጫዎችና ከአዲስ ኪዳን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ እንረዳለን።

1. እርሱ የእግዚአብሔር ባሪያ ይሆናል። ኢሳይያስ ስለ መሢሑ መምጣት ለመግለጽ አያሌ ቃላት ተጠቅሞአል። በ11፡1 «ቅርንጫፍ» እና «ሥር» የሚሉትን ቃላት ተጠቅሞአል። አሁን ደግሞ ለመሢሑ ሌላ ስያሜ በመስጠት «ባሪያ» ይለዋል። በዘካርያስ 3፡8 ወደፊት የሚመጣው መሢሕ «ባሪያ» እና «ቅርንጫፍ» ተብሎአል። ለብዙዎቻችን «ባሪያ» ወይም «አገልጋይ» የሚለው ቃል በጣም አሉታዊ ጽንሰ አሳብን ያንጸባርቃል። በመጽሐፍ ቅዱስም በሌላ አካል ቁጥጥር ሥር መዋልን ለማሳየት ሲባል ያገለገለ ቃል ነው።

ጳውሎስ ኢየሱስ ክርስቶስን ለማገልገል ሕይወቱን ሙሉ ለሙሉ እንደሰጠ ለመግለጽ የእግዚአብሔር ባሪያ መሆኑን ተናግሮአል። በዚህ ምንባብ ግን «ባሪያ» ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጥ ቃል አገልግሎቱን ያበረከተው ለየት ባለ መንገድ ነው። በጥንት ዘመን ይህ ቃል ንጉሡ ወደ ሌላ አገር የሚልከውን ልዩ የልዑካን ቡድን ወይም የንጉሡ የቅርብ ወዳጅ ሆኖ በንጉሡ ፋንታ የሚናገርን ወኪል ለማመልከት የሚያገለግል ቃል ነው። የንጉሥ የቅርብ ወዳጅና አማካሪ ሆኖ የንጉሥን መልእክት ማድረሱ ትልቅ ክብር በመሆኑ፥ «ባሪያ» የሚለው ስም የተከበረ ነበር። የሚመጣው መሢሕ እግዚአብሔርን በሁሉም ነገር በመወከልና አሳቡን ከሁሉም በላቀ መልኩ በማገልገል ከእግዚአብሔር ጋር ልዩና የቀረበ ግንኙነት ይኖረዋል። ፍጹም አገልጋይ በመሆን እግዚአብሔር ለሌላኛው አገልጋዩ ማለትም ለእስራኤል ያሰበውን ዕቅድ ከግቡ ያደርሳል።

2. እግዚአብሔር ደግፎ ይይዘዋል። መጭው ባሪያ ሰውም አምላክም ይሆናል። ስለሆነም የእግዚአብሔርን ብርታት ይሻል። እግዚአብሔር ያከናውነው ዘንድ የመረጠውን ተግባር ከዳር እንዲያደርስ ይረዳዋል።

3. የእግዚአብሔር ምርጥ ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን ለዓላማው እንደመረጠ ሁሉ (ኢሳ. 41፡8)፥ የሚመጣው የእግዚአብሔር ባሪያም ዕቅዶቹን ይፈጽም ዘንድ በእግዚአብሔር ይመረጣል።

4. እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት ይሆናል። በታሪክ ሁሉ እግዚአብሔር እንደ እስራኤል ወይም ዳዊት የመሳሰሉትን አገልጋዮች ፈቃዱን ይፈጽሙ ዘንድ መርጧል። እነዚህ ሁሉ አገልጋዮች በአንድ ወይም በሌላ መንገድ እግዚአብሔርን አስቀይመውታል። ጥሪያቸውን ተግባራዊ አላደረጉትም። ዳዊት እንኳ በኃጢአት ወድቆ የእግዚአብሔርን ፍርድ ተቀብሎአል። ይሁንና፥ መጭው የእግዚአብሔር ባሪያ ለእግዚአብሔር ሙሉ ደስታ በሚያመጣ መልኩ በመኖር አገልግሎቱን ያበረክታል። ይህም ማለት የሚያደርገው ሁሉ በእግዚአብሔር ትእዛዝትና ለእግዚአብሔር ክብር ይሆናል ማለት ነው (ዮሐ. 4፡34፤ 6፡38–39፤ 8፡29)።

5. የእግዚአብሔር መንፈስ ያርፍበታል። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር አንድን ልዩ መሪ በሚመርጥበት ጊዜ የመሪነቱን ተግባር ይወጣ ዘንድ መንፈሱን ያፈስበታል። (ለምሳሌ ሳምሶን፥ ሳሙኤል፥ ዳዊት)። መጭው የእግዚአብሔር ባሪያም የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ያርፍበታል። (ይህ ትንቢት የተፈጸመበትን ሁኔታ ከማቴዎስ 3፡13–16 ተመልከት።) ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተአምራትን አድርጓል (ማቴ.

12፡28)። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ለሰው ልጆች ኃጢአት የመሞቱን ተግባር እንዲያከናውን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሙሉ ለሙሉ አስታጥቆታል (ዮሐ. 8፡28)። ይኸው መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን እንዲገዛ ይረዳዋል።

6. ለአሕዛብ ፍርድን የሚያመጣው ይኸው ባሪያ ነበር። ከአዳምና ሔዋን ውድቀት ጀምሮ ለሕዝቡ ሙሉ ፍትሕ ያስገኘ አንድም መሪ አልነበረም። ነገር ግን የእግዚአብሔር ባሪያ የሆነው መሢሕ በሚመጣበት ጊዜ ይኼ ሁኔታ ይለወጣል። ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም አገሮች ሁሉ ፍትሕ ይሰፍናል። በእርሱ ፍርድ አማካኝነት አንድ ቀን ክፋት ተወግዶ ፍትሕ ዓለምን ያስተዳድራል። ዓለም ሁሉ በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር በመዋል በታዛዥነት ይኖራል።

7. አይጮኽም፤ ቃሉንም አያነሣም። የዓለም መሪዎች (ወላጆች ወይም ሌሎች የትኞቹም ዓይነት መሪዎች) ከአንድ ሰው ጋር በሚጣሉበት ጊዜ የመጀመሪያው እርምጃቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሰውዬው ላይ መጮኽ ነው። እነዚህ ሰዎች በኃይል የሚገዙ ሲሆን፥ የሚመጣው ባሪያ ግን የተለየ ይሆናል። ይህ ባሪያ በትሕትናና በጨዋነት ይመራል። ሙሉ ኃይልና ሥልጣን ስለሚኖረው መጮኽ አያስፈልገውም። የተሟላ ሰላምን ለዓለም ስለሚያመጣ የሚያናድድና የሚያስጮኽ ችግር አይገጥመውም፤ ኃይልና ማንነቱ ሰዎችን አያስደነግጥም፤ አይጨቁንም። ወይም በሰው ፊት መልካም መስሎ ለመታየትና አለበለዚያም ለመደነቅ ድምፁን አያነሣም። ይልቁንም በጸጥታና ማንንም በማይነካ መልኩ አገልግሎቱን ያበረክታል።

8. የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፤ የሚጤስንም ጣፍ አያጠፋም። በዕብራውያን ባሕል፥ አንድ ሰው የተቀጠቀጠን ሸምበቆ እንደማይሰብር መናገር የሰውየውን ደካማነት መግለጽ ነበር። ይህ ሸምበቆና ክር ማንን እንደሚመለከት ማወቁ አስቸጋሪ ነው። እነዚህ አገልጋዩን የሚያመለክቱ ናቸው? እንደዚህ ከሆነ፥ አገልጋዩ ሰው ሊቀመጥበት እንደማይችል በከፊል የተሰነጠቀ ሸምበቆ ዓይነት አካላዊ ገጽታ ይኖረዋል ማለት ነው። ሸንበቆ በተፈጥሮው ደካማ ሲሆን፥ የተቀጠቀጠ ሸንበቆ ደግሞ በመጉበጥና በመሰንጠቅ ኃይሉን እንዲያጣ የተደረገ ነው። ወይም ደግሞ ሊጠፋ እንደተቃረበና ዳሩ ግን ጭል ጭል የሚል ብርሃን እንደሚሰጥ ጧፍ ይሆናል። በተመሳሳይ ሁኔታ የሚመጣው አገልጋይ ብርቱ መስሎ አይታይም። እንዲያውም የተቀጠቀጠና ሊጠፋ የተቃረበ ብርሃን ይሆናል። እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ኢሳይያስ በምዕራፍ 53 በስፋት የገለጸውን የመሢሑን ሥቃይና ሞት ይገልጻሉ። ሌሎችን ለመቆጣጠርም ኃይልን በመሣሪያነት አይጠቀምም። ደካማ ስለሚመስል ደካሞችና የሥቃይ

ሰዎች ታላቅ የመጽናናት ምንጭ ሆኖ ያገኙታል። ሌሎችን ከማፈራረስ ይልቅ የፈራረሰ ሕይወታቸውን ይጠግናል።

ወይስ የተቀጠቀጠ ሸንበቆ አገልጋዩ የሚረዳቸውን ሰዎች ያመለክት ይሆን? አገልጋዩ ሕይወታቸው የፈራረሰውን፥ ተስፋ–ቢስነት የተጫናቸውን፥ ብልሹ ግብረገባዊ ሕይወት በመላበስ በመንፈሳዊ ዝለት የነሰቆሉትንና የመጊሔን ነፃ የማውጣት እገዛ የሚጠይቁትን ለመርዳት እጁን ይዘረጋላቸዋል። ሁለቱም አተረጓገሞች ሊሆኑ የሚችሉ ሲሆን፥ ሁለተኛው ግን ይበልጥ ተስማሚ ነው።

9. በታማኝነት ይሠራል። አብዛኛዎቹ መሪዎች ለሕዝቦች ስለሚያደርጓቸው ሰናይ ነገሮች የተስፋ ቃል ይገባሉ። ይሁንና፥ ዓቅም ስለሚያጥራቸው ይሁን ወይም ወደ መሪነቱ ከመጡ በኋላ ስለሚለወጡ የገቡትን የተስፋ ቃል አይፈጽሙም። የገቡትን የተስፋ ቃል ለመፈጸም ታማኞች አይሆኑም። የሚመጣው የእግዚአብሔር ባሪያ ግን ያለምንም ውሸት ወይም የማይፈጸም የተስፋ ቃል ባለመስጠት እግዚአብሔርን በታማኝነት ያገለግላል። የሚሠራው ሁሉ በታማኝነትና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ይሆናል። ለቃሉቹና ለሕዝቡ ለሚገባቸው ተስፋዎች ታማኝ ይሆናል። በፍትሕ በመሥራት ለሕዝቡ ፍትሕን እንደሚያመጣ የተናገረውን ይፈጽማል።

10. በኢሳይያስ 40 ከተጠቀሱት ብላቴኖች በተቃራኒ፥ የእግዚአብሔር ባሪያ አይታክትም፤ ተስፋ አይቆርጥም። ብዙ መሪዎች በጥሩ ሁኔታ ሥራቸውን ይጀምሩና ከመሪነት ውጥረቶች ሳቢያ ይዝላሉ። ዕቅዶቻቸው በሚፈልጉት ፍጥነትና አኳኋን ሳይፈጸሙ ሲቀሩም ተስፋ ይቆርጣሉ። መጊሔ ግን እንዲህ አይሆንም። እርሱ አምላክ ስለሆነና ዕቅዶቹ ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ስለሚፈጸሙ አይደክምም ወይም ተስፋ አይቆርጥም። ይልቁንም የመጊሔ የመጨረሻ ሥራዎችና ዕቅዶች የጠበቁና ለተፈጻሚነታቸው ምንም ጥርጥር የሌለባቸው ናቸው። እንደ ባቢሎን፥ አሦር፥ አሜሪካና ሩሲያ ከመሳሰሉት ኃያላን አገሮች አንሥቶ እጅግ ርቆ እስከሚገኙት አናሳ ደሴቶች ድረስ አገሮች ሁሉ በጽድቅ ይመራሉ። የፍትሕን ምንነት የሚበይነው የእግዚአብሔር እንጂ የሰዎች ሕግ አይሆንም። ዓለም በመጨረሻው በፍትሕ የምትገዛ መሆኗ የመጨረሻውን ድህ ሳይቀር የሚያጽናና ተስፋ ነው።

ይህ ማለት ግን መጊሔ ከጎጂ ሥቃይና ውጥረቶች ነፃ ነው ማለት አይደለም። ጉዳቶች ይገጥሙታል። ነገር ግን ከሚጋፈጣቸው ሥቃዮችና ችግሮች ባሻገር እግዚአብሔር የሰጠውን ተግባር መፈጸሙን ይቀጥላል። እግዚአብሔርን ለመከተል ያለው ውስጣዊ ቁርጠኝነቱ

ከዝለትና ተስፋ ከመቁረጥ ይጠብቀዋል። ደቀ መዛሙርቱ በሚተዉትና መስቀሉን በሚጋፈጥበት ጽልመታም ወቅት እንኳ ተስፋ አይቆርጥም።

22ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ከዚህ የእግዚአብሔር ባሪያ ሕይወት ለአሁንም ሆነ ለወደፊት ተስፋ የሚሰጡህ ነገሮች የትኞቹ ናቸው? ለ) ከዚህ ምንባብ ስለ መጪረሻው ዘመን ምን እንማራለን? ሐ) ይህ የእግዚአብሔር ባሪያ ዛሬ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊከተሉት የሚገባው የመሪነት ሞዴል የሆነው እንዴት ነው? መ) ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ክፍል የፈጸመባቸውን መንገዶች ግለጽ።

በማቴዎስ 12፡18–21 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር ባሪያ የተነገረውን ይህንኑ ትንቢት እንደፈጸመ ተገልጾአል። መሢሑ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም የእግዚአብሔር ባሪያ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት እነዚህ ባሕርያት በአብዛኛው በእርሱ ላይ ደምቀው ይታዩ ነበር–በእግዚአብሔርና በመንፈስ ቅዱስ መቀባቱ፥ የታመሙትን፥ ሌሎች የናቁዋቸውን ኃጢአተኞች፥ ወዘተ... ማጽናናቱ፥ ድሆችንና ኃያላንን ነጣጥሎ ያልተመለከተበት ፍትሕ ለዚህ በዋቢነት የሚጠቀሱ ናቸው። ነገር ግን ከእነዚህ ትንቢቶች አንዳንዶቹ ገና ወደፊት የሚፈጸሙ ናቸው። ይኸውም አንድም (የቅድመ–ሺህ–ዓመታት አመለካከት ያላቸው ወገኖች እንደሚሉት) ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲነግሥ አልያም (አልቦ–ሺህ–ዓመታውያንና ድህረ–ሺህ–ዓመታውያን እንደሚሉት) በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥተ ሰማይ በዘላለም መንግሥት የሚፈጸሙ ይሆናሉ።

ለ. ለባሪያውና ለሕዝቡ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል (ኢሳ. 42፡5–9 አንብብ)

የልዩ አገልጋዩን ባሕርያት ከገለጸ በኋላ እግዚአብሔር ወደ አገልጋዩ በማመልከት ቀጣይ ዓለም አቀፍ አገልግሎቱ ምን እንደሚሆንና እግዚአብሔር የወጠነውን ዕቅድ እንደሚፈጽም ቃል ገብቶአል። እግዚአብሔር ራሱን ፈጣሪ በማለት ጠርቶአል። ይህም በሰዎች ላይ ሙሉ መብት እንዳለውና ሊሰሙት እንደሚገባ የሚያሳይ መልእክት ነው። ልዩ አገልጋዩን እንደሚልክ ከተናገረ በኋላ እግዚአብሔር ሁለት ዓይነት ሰዎችን ጠቅሶአል።

1. በምርኮ ያሉትን አይሁዶች በመጥቀስ በተዘዋዋሪ መንገድ ስለ አሕዛብና ጣዖቶቻቸው ገልጾአል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ታላቅነቱን ለማሳየት ስለፈለገ ኢሳይያስ እግዚአብሔርንና ጣዖታትን ያነጻጸረበትን የምዕራፍ 41ን ጭብጥ ደግሞ አቅርቦአል። እግዚአብሔር ለአይሁዶች እርሱ የሰማይ ሁሉ አምላክ እንደሆነ ገልጾአል። አንድ ሰው ድንኳን ለሰርግ እንደሚዘረጋ ሁሉ እግዚአብሔርም ሰማያትንና በውስጡ ያሉትን ሁሉ ዘርግቶአል። ለሰዎች ሁሉ ሕይወትን

የሚሰጣቸው (እስትንፋስ የሕያውነት ምልክት ነው) እና በምድር ላይ እንዲመላለሱ የሚያስችላቸው እግዚአብሔር ነው። ሕይወትን ሁሉ የሚያኖረው እርሱ ስለሆነ እግዚአብሔር የሚያስበው ለአይሁዶች ብቻ ሳይሆን ለፈጠራቸው ሰዎች ሁሉ ነው።

2. ቀጥሎ ስለ ባሪያው ማለትም ስለ መሢሑ ተናግሮአል።

ሀ) እግዚአብሔር በጽድቅ እንደጠራው ለባሪያው ገልጾለታል። በዚህ ስፍራ «ጽድቅ» የሚለው ቃል እግዚአብሔር ከወሰነው መመዘኛ ጋር የሚስማማ ማለት ነው። እግዚአብሔር በጽድቅ አማካኝነት ለዓለም ፍትሕን ስለሚያመጣ (ኃጢአተኞችን በመቅጣትና ጻድቃን የእግዚአብሔርን ሕግጋት ይፈጽሙ ዘንድ ልባቸውን በመለወጥ) አገልጋዩን መጥራቱ ትክክል ነው። ይህ እግዚአብሔር ቂሮስን በመጥራት ባቢሎንን አሸንፎ ሕዝቡን ነፃ እንዲያወጣ ካደረገበት የጽድቅ ጥሪ ጋር ተመሳሳይ ነው (ኢሳ. 41፡2)።

ለ) በተጨማሪም እግዚአብሔር ለመሢሑ እጁን ይዞ እንደሚመራውና ተሰናክሎ እንደማይወድቅ ገልጾለታል። ይህም እስራኤላውያን ከምርኮኛነት በሚወጡበት ጊዜ አብሮአቸው እንደሚሄድ ከተናገረበት የተስፋ ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው (ኢሳ. 41፡13)። የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ቀላል አልነበረም። ለዚህ ነው ብዙውን ጊዜ በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ሲገናኝ የነበረው። ለዚህም ነው በመጨረሻው እግዚአብሔር ከፈቀደ ጽዋውን እንዲወስድለት የጠየቀው። እግዚአብሔር የመሢሑን መንገድ ቀላል ባያደርገውም በሥራው ሁሉ አብሮት ነበር።

ሐ) እግዚአብሔር መሢሑን ለሕዝብ ቃል ኪዳን ያደርገዋል። እግዚአብሔር በዚህ አገልጋዩ አማካኝነት የብሉይ ኪዳንን ቃል ኪዳኖች ሁሉ ይፈጽማል። እነዚህም ቃል ኪዳኖች ከአብርሃም (ዘፍጥ. 12፡1–3)፥ ከእስራኤል (ዘጸ. 19)፥ እና ከዳዊት (2ኛ ሳሙ. 7፡1–16) ጋር የተያረጉት ናቸው። በተጨማሪም እግዚአብሔር በመሢሑ አማካኝነት ከሕዝቦች ጋር አዲስ ቃል ኪዳን ያደርጋል (ዕብ. 9፡11–27)። ይህ ቃል ኪዳን ከአይሁዶች ጋር ብቻ ሳይሆን ከሰዎች ሁሉ ጋር የሚደረግ ነው።

መ) ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ እሰጥሃለሁ። ኢሳይያስ ብርሃንን ከደኅንነት ጋር አመሳስሎ ይጠቀማል (ኢሳ. 49፡6)። የእግዚአብሔር ባሪያ ደኅንነትን የሚያመጣው ለአይሁዶች ብቻ ሳይሆን ለሰዎች ሁሉ ነው። መጀመሪያ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያቀደውን ዕቅድ በመፈጸም አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር እንዲመጡ ያደርጋል። ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞቱና ወንጌሉ በዓለም ሁሉ በመታወጁ፥ ይኼ ዛሬም ሳይቀር እየተፈጸመ ያለ ክስተት ነው።

የመጨረሻው ፍጻሜ የሚሆነው መሢሑ በሰዎች ሁሉ ላይ ሲነግሥና እነርሱም በሕልውናው ብርሃን ደስ ሲሰኙ ነው።

ሠ) የዕውሮችን ዓይኖች በመክፈትና ምርኮኞችን በመመለስ አገልጋዩ የእግዚአብሔርን ዕቅዶች ይፈጽማል። ኢሳይያስ መጽሐፉን የጀመረው የእስራኤላውያን ዓይኖች እንዴት ለመንፈሳዊ ነገሮች እንደታወሩ በመግለጽ ነበር (ኢሳ. 6፡9–10)። እግዚአብሔር እነዚህ መንፈሳዊ ዓይኖች እንደሚከፈቱና ሕዝቡ የእግዚአብሔርን እውነት እንደሚያይ በተደጋጋሚ ተናግሯል (ለምሳሌ፥ ኢሳ. 29፡18፤ 32፡3፤ 35፡5)። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ የሰዎቹን መንፈሳዊ ዓይኖች ከፍቶአል። ዛሬም እንኳ በመንፈስ ቅዱስ ሥራ መንፈሳዊ ዓይኖች እየተገለጡ ናቸው (ኤፌ. 1፡18)። በመጨረሻው ዘመን መንፈስ ቅዱስ ከዚህም በሚበልጥ መንገድ በመሥራት በዓለም ዙሪያ የአይሁዶችንና የአሕዛብን ዓይኖች ይከፍታል። ይህም ሲሆን፥ ዓለም ሁሉ አገልጋዩን ኢየሱስ ክርስቶስን ያከብራል። በተጨማሪም መሢሑ የሕዝቡን ሥጋዊ ዓይኖች ይከፍታል። በሉቃስ 4፡18 ኢየሱስ ክርስቶስ ዓይነ ስውራን የነበሩትን ሰዎች በመፈወስ ይህንን ትንቢት እንደፈጸመ እናነባለን።

ይህ አገልጋይ ሰዎችን ከምርኮኝነትም ነፃ አውጥቶአቸዋል። አይሁዶች በባቢሎን ታስረው ከነበሩበት ፖለቲካዊ ምርኮኝነት ተለቅቀዋል። በታሪክ ሁሉ አይሁዶችም ሆኑ ሌሎች የሰው ዘሮች የማቀቁባቸው ፖለቲካዊ እስራቶች ነበሩ። መሢሑ ለመግዛት በሚመጣበት ጊዜ ይህ ሁሉ ገጠመኝ ይወገዳል። በተጨማሪም ሰዎች ለሰይጣንና ለኃጢአት የሚገዙበት ሥነ ምግባራዊ ምርኮኝነትም አለ። በመስቀል ላይና በሚያምኑት ሰዎች ሕይወት በሚሠራው መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት መሢሑ ተከታዮቹን ከኃጢአትና ከሰይጣን ባርነት ነፃ ያወጣል። መንፈሳዊ ጨለማቸው ተገፍፎ በወንጌሉ ብርሃንና ይኸው ብርሃን በሚያመጣላቸው ደስታ ሐሤት ያደርጋሉ።

23ኛ ጥያቄ፡– መሢሑ ዓይኖችህን የከፈተውና ከምርኮኝነት ነፃ ያወጣህ እንዴት ነው? አሁን ለዚህ ተግባሩ ታመሰግነው ዘንድ ጊዜ ውሰድ።

እግዚአብሔር አሁንም አሕዛብንና ጣዖቶቻቸውን ተገዳድሯል። ስለ ወደፊት ክስተቶች የተነበዩት የት ጋ ነው? ሕዝቡን ከምርኮ ለማውጣት ችለው ነበርን? እግዚአብሔር እንዲፈጸም ያልፈቀደው አንድ ነገር ቢኖር ክብሩን ለሌሎች መስጠት ነው። አይሁዶች ጣዖታት ከምርኮኝነት እንደሚያወጧቸው ቢያምኑ፥ ያ የእግዚአብሔርን ክብር ለጣዖታት አሳልፎ እንደመስጠት ነበር። እግዚአብሔር ግን እነዚህ ጣዖታት ምንም ያህል ብቃት የሌላቸው እንደሆኑ አመልክቷል። ዕቅዶቹ ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ ታሪክን የተቆጣጠረው እርሱ ነበር።

መሢሑ ዓለምን እንዲገዛ መላኩን ጨምሮ አዳዲስ ነገሮችን የሚሠራው እርሱ ነበር። እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካኝነት ወደፊት የሚሆነውን የተነበየ ሲሆን፥ ታሪክን በመቆጣጠሩ ክስተቶቹ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ በምድር ላይ በኖረበት ወቅት በመቶዎች የሚቆጠሩ ትንቢቶች እንደ እግዚአብሔር ቃል ተፈጽመዋል። እነዚህ ሁሉ ጣዖታት ምንም ኃይል እንደሌላቸው ያሳያሉ። ኃይል የእግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለሆነም ሕዝበ-እግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ብቻ የሚገባውን ክብር ለሌሎች ሊሰጡ አይገባም።

እግዚአብሔር ክብሩ ለማንም እንዲሰጥበት አይፈልግም። በሐዋርያት ሥራ 12፡19-23 ቀዳማዊ ንጉሥ አግሪጳ ራሱን እንደ አምላክ አድርጎ የገለጸበትን ሁኔታ እንመለከታለን። ወዲያው የእግዚአብሔር ፍርድ በእርሱ ላይ ወርዶ ሊሞት በቅቷል። ክርስቲያኖች የመዘመር ችሎታቸው ከራሳቸው እንደመጣ በማሰብ ከሰዎች የሚቀርብላቸውን ክብር ለራሳቸው ሲቀበሉ ይህንኑ በደል ይፈጽማሉ። ወይም ደግሞ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የመለሱት በራሳቸው ብቃት እንደሆነ በልባቸው ሲያስቡና ለሌሎችም ሲናገሩ ይህንኑ በደል ይፈጽማሉ። አገልጋዮች ሆነን በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የምንሠራ ሰዎች የእግዚአብሔርን ክብር እንዳንወስድ ልንጠነቀቅ ይገባል። ይህንን ካደረግን እንደሚፈርድብንና እንደሚያዋርደን ግልጽ ነው።

24ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ክብር ለራሳቸው የሚወስዱባቸውን ወይም ለሌሎች የሚሰጡባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) እግዚአብሔር ይህንን በሚያደርጉት ላይ ሲፈርድ የተመለከትኸው እንዴት ነው?

2. ለእግዚአብሔር የምስጋና መዝሙር (ኢሳ. 42፡10-17 አንብብ)

ሀ. እግዚአብሔር በምድር ላይ በሚሠራበት ጊዜ የሚዘምሩና የሚደሰቱ ሰዎች (ኢሳ. 42፡10-12 አንብብ)

እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በሚሠራበት ጊዜ ሥራው ለተቀደሰው ስሙ ምስጋናን ያመጣል። እግዚአብሔር በሙሴ መሪነት እስራኤላውያንን ከግብፅ ባወጣ ጊዜ እስራኤላውያን ታላቅ ምስጋና አቅርበውለታል (ዘጸ. 14፡29-15፡21)። በዚህ ወቅት እግዚአብሔር ሕዝቡን ከባቢሎን ምርኮ ሊያወጣቸው ዐቅዶ ነበር። ይህም በመጨረሻው ዘመን መሢሑ በሚመጣበት ጊዜ ከዓለም አገሮች ሁሉ ሕዝቡ ነፃ የሚወጡበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነበር።

እግዚአብሔር በምድር ላይ በሚሠራበት በዚያን ታላቅ ቀን የእግዚአብሔርን አዲስ ተግባር በማመልከት አዲስ መዝሙር ይዘመራል። እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡ ጊዜ የሙሴ እኅት ማርያም

እንደዘመረችው፥ የእግዚአብሔርም ሕዝብ በመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔርን ነፃ ማውጣት በሚመለከቱበት ጊዜ ሌላ መዝሙር ይዘምራሉ። አዲስ የሆነበትም ምክንያት እግዚአብሔር ቀደም ሲል ያደረገላቸውን ሳይሆን የወቅቱን ሁኔታ በማሰብ የሚዘምሩት በመሆኑ ነው። ኢሳይያስ ከዓለም ሁሉ እነዚህ መዝሙሮች የሚመጡባቸውን ስፍራዎች ዘርዝሯል።

ሀ. የምድር ዳርቻ–ሰዎች ባሉበት ስፍራ ሁሉ።

ለ. የባሕር–ነጋዴዎች በታላላቅ መርከቦች የሚጓጓዙባቸው ስፍራዎች

ሐ. ደሴቶች–በዓለም ዙሪያ ርቀው የተበተኑ ሕዝቦች፤ እግዚአብሔር ግን በታላላቅ የዓለም አገሮች እንዳደረገው በእነዚህም ስፍራዎች ይሠራል።

መ. ምድረ በዳዎች – በዘላንነት የሚኖሩ ጥቂት ሰዎችም እግዚአብሔርን ለማመስገን ምክንያት ይኖራቸዋል።

ሠ. ከተሞች–ብዙ ሰዎች የሚኖሩባቸው የሥልጣኔ ስፍራዎች

ረ. የቄዳር አካባቢዎች–እነዚህ በዓረቢያ አካባቢ ዘላኖች የሚኖሩባቸው ቦታዎች ናቸው። ይህ ስፍራ ዛሬ በሙስሊሞች ቁጥጥር ሥር ይገኛል። ኢሳይያስ ይህንን ስፍራ የጠቀሰው እግዚአብሔር ርቀው በሚገኙትና ሰዎች በሚፈሩዋቸው ተዋጊ ጎሳዎች መካከል ጭምር እንደሚሠራ ለማመልከት ነው።

ሰ. ሴላ–ይህች የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች የሆኑት ሞዓባውያን የሚኖሩባት ርእሰ–ከተማ ነች። ሞዓብ የክፉ አገሮች ሁሉ ተምሳሌት እንደሆነች ቀደም ብለን ተመልክተናል። አንድ ቀን ግን እግዚአብሔር በሕዝቡ ታሪካዊ ጠላቶች መካከል ሳይቀር በመሥራት ለዘላለማዊ ስሙ ምስጋናን ያመጣል። ሴላ ለእግዚአብሔር ላለመገዛት የወሰኑ የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪካዊ ጠላቶች ተምሳሌት እንደሆነች አይጠረጠርም። ነገር ግን አንድ ቀን እግዚአብሔር በእነርሱም መካከል በመሥራት የምስጋና መዝሙር እንዲዘምሩ ያደርጋል።

ለ. ተዋጊው አምላክ ሕዝቡን ከዓለም ዙሪያ ስለሚታደግ ሕዝቡ በምስጋና ያዜማሉ (ኢሳ. 42፡13–17 አንብብ)

በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ ከሚገኙት ዐበይት መግለጫዎች አንዱ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደሚዋጋላቸው ነው። የአይሁዶችን ከባቢሎናውያን እጅ ነፃ መውጣትና በተለይም ደግሞ በመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁሉ ነፃ የሚወጡበትን ሁኔታ በማጤን፥ ኢሳይያስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ለመዋጋት ከሠራዊቱ ፊት

ፊት እንደሚገሠግሥ ጦረኛ አድርጎ ገልጾታል። ይህም ዳዊት ጎልያድን ለመዋጋት በሕዝቡ ፊት ቀድሞ የወጣበትን ሁኔታ የሚመስል ነው።

በተጨማሪም ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ዘጠኝ ወራት በሙሉ ልጅ ለመውለድ በትዕግሥት ስትጠባበቅ እንደቆየች ድርስ እርጉዝ አድርጎ ገልጾታል። እግዚአብሔርም ከአዳምና ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ ዕቅዶቹን ለዓለምና ለፈጠራቸው ሰዎች የሚፈጽምበትን ጊዜ በትዕግሥት ሲጠባበቅ ቆይቷል። እግዚአብሔር የዓለምን ኃጢአትና መከራ ለማብቃት ጣልቃ ሊገባ የፈለገባቸው ጊዜያት ቢኖሩም፥ በትዕግሥት ሲጠባበቅ ቆይቷል። ይህንንም ያደረገው ሰዎች እንዲድኑ እንጂ እንዳይጠፉ ዕድል ሊሰጣቸው ስለፈለገ ነው (2ኛ ጴጥ. 3፡1–10 ተመልከት)። ጊዜው ሲደርስ እግዚአብሔር በምድር ዙሪያ እንደ ተዋጊ በመንቀሳቀስ አዲሱን ምዕራፍ ሊከፈት በላቀ ኃይል ይነሣል። እግዚአብሔር ጠላቶቹን ለመደምሰስና መሰናክሎችን ሁሉ ለማሸነፍ የሚያስችል ግዙፍ ኃይል እንዳለው ለማመልከት ኮረብቶችንና ተራሮችን እንደሚያፈራርስ ተገልጾአል። ክፋትን ሁሉ በሚዋጋበት ጊዜ ዕፅዋት ሁሉ ይቃጠላሉ። ጠላቶቹ ሁሉ ይደመሰሳሉ። በተለይም ኢሳይያስ በጣዖት በሚታመኑ ላይ ትኩረት አድርጓል። አሁንም ኢሳይያስ በምርኮ የነበሩት አይሁዶች በማይታየው አምላክ ላይ የነበራቸውን እምነት አጥተው ወደ ጣዖታት እንዳይመለሱ እያስጠነቀቃቸው መሆኑን እንረዳለን። ሌሎችን የዓለም ሃይማኖቶች የተከተሉ ሰዎች ለጥፋት ይጋለጣሉ እንጂ ተዋጊው እግዚአብሔር ከሚፈጽመው ነፃ የማውጣት ተግባር ተጠቃሚ አይሆኑም።

እግዚአብሔር ለእርሱ ለሚታመኑትና በተለይም ደግሞ ለደካከሙት በመዋጋት ነፃ ያወጣቸዋል። እግዚአብሔር ዕውሩን ይመራዋል። ይህ እግዚአብሔርን ያለመታዘዝ ባሕል ያዳበሩትን እስራኤላውያን ለመግለጽ ያገለገለ አሳብ መሆን አለበት። ምክንያቱም ኢሳይያስ ይህንኑ አለመታዘዛቸውን ለማመልከት ዕውሮች እንደሆኑ በተደጋጋሚ ሲናገር ነበርና (ኢሳ. 42፡18–19 አንብብ)። እንዲያውም ለብዙ መቶ ዓመታት የእግዚአብሔርን ቃል ሰምታ ስታበቃ ንስሐ በመግባት እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመኖር ያልቻለችው እስራኤል ይህንኑ ምስክርነት ካላገኙት አሕዛብ በላይ ዕውር ነበረች። ይህ በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ አድገው ለእግዚአብሔር ቃል ከማይገዙትና ራሳቸውን ለኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፈው ከማይሰጡት ልጆች ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው። የእነዚህ ልጆች ልብ ወንጌሉን ሰምተው ከማያውቁት ሰዎች በላይ ድድር ነው።

አንድ ቀን ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት እስራኤላውያን ተለውጠው ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ይመላለሳሉ። እግዚአብሔር በቀዳሚነት ከባቢሎን ምርኮ በመመለስና ወደ ይሁዳ በመምራት

ይታደጋቸዋል። በዚህ ጊዜ አዲስ የአይሁዳውያን ትውልድ መወለዱ ስለማይቀር ወደ እስራኤል የሚኬድበትን መንገድ ላያውቁ ይችላሉ። እግዚአብሔር ግን መንገዱን ያሳያቸዋል። በዕዝራ 1፡1–8 እግዚአብሔር የማያምኑትን ሰዎች ልብ እንዴት እንዳነሣሣና አረማዊ ንጉሥ አይሁዶች ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው እንዲቋቋሙ ገንዘብ እንዲሰጣቸው እንዳደረገ እናነባለን። በተጨማሪም እግዚአብሔር በአዲስ መንገድ እየመራ መንፈሳዊ ዕውርነታቸውን በማስወገድ፥ መንገዳቸውን እያበራና መሰናክሎችን እያነሣ እርሱን የሚከተሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት ይጠብቃቸዋል።

በዋነኛነት ትንቢቱ በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር አይሁዶችን ሁሉ ከአሕዛብ አገሮች አውጥቶ ወደ ይሁዳ የሚመልስበትን ሁኔታ የሚያመለክት ይመስላል። (ማስታወሻ፡ ዛሬ በዓለም ዙሪያ ተበትነው የሚገኙ አይሁዶች በምድረ እስራኤል ካሉት ይበዛሉ። ነገር ግን ከእነዚህ ከተመሳሳይ ትንቢቶች እንደሚታየው ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱ አይሁዶች አሁን ካሉባቸው አገሮች ለቅቀው ወደ አብርሃም ምድር የሚመለሱ ይመስላል።)

3. ሕዝበ–እግዚአብሔር እግዚአብሔርን እንዲታዘዝ የቀረበ ማስጠንቀቂያ (ኢሳ. 42፡18–25 አንብብ)

ለሰዎች ስለ መጨረሻው ዘመን በረከት፥ ስለ መንግሥተ ሰማይና እግዚአብሔር በዚያ እያከናወናቸው ስላላው ተግባራት መናገሩ መልካም ነው። አንድ ቀን ነገሮች የተሻለ መልክ እንደሚኖራቸው በመገንዘብ ሊጽናኑ ይገባል። ነገር ግን እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ ለመኖር ከመረጡ ምን ሊደርስባቸው እንደሚችል ማስጠንቀቁም ከማጽናናቱ እኩል አስፈላጊ ነው። መልካሙ ዜና በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ የዘላለም ሕይወት የሚጠብቃቸው መሆኑ ነው። ክፉው ዜና በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምኑ ሰዎች ለዘላለም የሚጠፉ መሆናቸው ነው። ኢሳይያስ ተዋጊ አምላክ የሆነው መሢሕ ለሕዝቡ ምን እንደሚያደርግ ካመለከተ በኋላ፥ አይሁዶች የእግዚአብሔርን ትእዛዛት እንዳይጥሱ አስጠንቅቆአቸዋል። ኢሳይያስ ትንቢቱን የጻፈው ከምርኮው ከአንድ ምእተ ዓመት አካባቢ በፊት ስለሆነ የሚያስጠነቅቀው እርሱ በኖረበት ዘመን የነበሩትን አይሁዶች ነበር። ነገር ግን በዓለም ሁሉ ተበትነው በምርኮኛነት የሚኖሩ አይሁዶችም እግዚአብሔርን በጥንቃቄ እንዲከተሉ አስጠንቅቋቸዋል። ሕዝበ–እግዚአብሔር ለእግዚአብሔር ቃል ዓይናቸው ሲታወርና ጆሮአቸውን ነፍገው ለመንፈሳዊ ደንቆሮነት ሲዳረጉ፥ የዓለም ሕዝቦች የእግዚአብሔርን ቃል ለመከተል ይቸገራሉ። ይህ ዛሬ ለእኛም ጥሩ ማስጠንቀቂያ ነው። ክርስቲያኖች ነን ብንልም እንኳ እግዚአብሔርን

የሚታዘዝ ንጹሕ ሕይወት ከሌለን የእግዚአብሔርን ፍርድ ከመጋፈጥ አናመልጥም።

አይሁዶች የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንዲሆኑ በእርሱ ተመርጠው ነበር። ኢሳይያስ «የጽድቅ» እና «ታላቅና ክቡር» ሲል የገለጸው ቃለ-እግዚአብሔር ተሰጥቶአቸዋል። ኢሳይያስ በሲና ተራራ ለሙሴ ስለተሰጡት ሕግጋት እያስታወሰ መሆኑ አያጠራጥርም (ዘጸ. 19-20)። ከኃጢአተኛ አሕዛብ ጋር ሲነጻጸሩ ጻድቃን የነበሩት የእግዚአብሔር ሕዝብ ያ ሕግ ምን ያህል የተለየ እንደሆነ ሊገነዘቡና ሕጉን በመታዘዝ ሊመላለሱ ይገባ ነበር። የሚያሳዝነው ግን የተገላቢጦሹ እውን ሆነ። መንፈሳዊ ዕውርነትን ተላብሰው የእግዚአብሔር ሕግጋት ምን ያህል መልካም እንደሆኑና ለራሳቸው ጥቅም እንደተሰጡ መገንዘብ ተሳናቸው። በታሪካቸው ሁሉ እግዚአብሔር በካህናትና በነቢያት አማካኝነት ሊያናግራቸው ሲፈልግ ለደንቆሮነት ተዳርገው ድምፁን ለመስማት ሳይችሉ ቀሩ። ለብዙ መቶ ዓመታት እግዚአብሔር የሕዝቡን ልብና ሕይወት ለመለወጥ ያደረጋቸው ጥረቶች መና ቀሩ። እግዚአብሔር ሕዝቡ እንደሆኑ ሲናገሩ የነበሩት ሰዎች ሕጉን ካልተቀበሉት አሕዛብ በላይ ደንቆሮዎች እንደነበሩ በግርምት ተናገረ! (በኢሳይያስ 42፡25 «እርሱ» የሚለው እስራኤላውያንን የሚያመለክት ነው።)

የእግዚአብሔርን ቃል ሳይሰሙ፥ ሳይረዱና ሳይታዘዙ ሲቀሩ ምን ተከሰተ? የእግዚአብሔር ፍርድ ወረደባቸው! ባቢሎን ስትወራቸው ደግሞ ከዚያ የከፋ ይሆን ነበር። የእግዚአብሔር ባሪያዎች የሆኑት አይሁዶች ተበዝብዘው ለምርኮኛነት ይሰጣሉ። ወደፊት ከመቶ ዓመት በኋላ ለሚኖሩት አይሁዶች ሲናገር፥ ኢሳይያስ፥ «ይህንን ያደረገው ማን ነው? የባቢሎንን ምርኮ ያመጣው ማን ነው?» ሲል ይጠይቃቸዋል። ይህ የሆነው የአሕዛብ አማልክት የበለጠ ኃይል ስለነበራቸው ነው? ወይስ ባቢሎን ከይሁዳ የበለጠ ኃይል ስለነበራት ነው? አይደለም! ኢሳይያስ ጥያቄ መልሱ እግዚአብሔር ነበር። እያወቁ በገዛ ፈቃዳቸው ትእዛዛቱን ለመጠበቅ ባለመፈለጋቸው አይሁዶችን ወደ ምርኮኛነት የሰደደው እግዚአብሔር ነበር። የእግዚአብሔር ቁጣ ያጠፋቸው ዘንድ እንደ እሳት ነበልባል በሕዝቡ ላይ ወረደ። ነገር ግን በምርኮ ውስጥ ሆነው እንኳ አይሁዶች ይህንን ውድመት ማን እንዳመጣው ወይም ለምን እንደመጣባቸው አላወቁም ነበር። በታሪክ የእግዚአብሔርን አሠራር ባለማወቃቸው እግዚአብሔር ሊያስተምራቸው የፈለገው አሳብ አልተገለጸላቸውም ነበር። (ማስታወሻ፡ ኢሳይያስ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ስለሆኑት እስራኤላውያን አለመታዘዝ ሲገልጽ በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ባሪያ ሕዝበ-እስራኤል ሳይሆን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ እያመለከተ ነበር።)

በተመሳሳይ ሁኔታ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያደጉ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ግልጽ ግንዛቤ እንደሚኖራቸውና የቃሉን እውነታ በማየት ራሳቸውን እንደሚቀርጹበት ተስፋ እናደርጋለን። አንዳንድ ጊዜ ግን የዚህ ተገላቢጦሽ ይከሰታል። በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ያደጉ ልጆች በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ማለት ምን እንደሆነ በትክክል ላይገነዘቡ ይችላሉ። እነርሱም ቢሆኑ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል የግል ውሳኔ ሊያደርጉ ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን እንደ እስራኤላውያን ለመንፈሳዊ ዕውርነት አልፈው ይሰጣሉ።

25ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ዛሬ ክርስቲያኖች ለእግዚአብሔር ዕውርና ደንቆሮ ሊሆኑ የሚችሉባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? ለ) እግዚአብሔር የሚያስጠነቅቃቸው እንዴት ነው? ሐ) አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር የሚቀጣቸው እንዴት ነው? መ) ምእመኖቻችን እንደ እስራኤላውያን እንዳይሆኑብን መሪዎች የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሳንጨምርባቸውና ሳንቀንስባቸው በትክክል ልናስተምር የሚገባን ለምንድን ነው? ሠ) ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደፊት የሚያገኘውን ደስታ ብቻ ሳይሆን ለመታዘዝ ባልፈለጉት ላይ የሚደርሰውን ቅጣት ጭምር እንዲያውቁ ለማድረግ በቤተ ክርስቲያን የምትወስደው እርምጃ ምንድን ነው?

አራተኛ ቀን፤ የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ውይይት ተዘጋጅ።

ሳምንታዊ ስብሰባ

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሀ) በኢሳይያስ ምዕራፍ 40 እግዚአብሔር በምርኮ ያሉትን እስራኤላውያን ያጽናናቸው እንዴት ነው? ለ) ዛሬ ክርስቲያኖች የሚጋፈጧቸው ተስፋ እንዲቆርጡና ከእምነታቸው እንዲያፈገፍጉ የሚያደርጉ አንዳንድ ሁኔታዎች ምንድን ናቸው? ሐ) ቀደም ሲል ካካሄድነው የትንቢተ ኢሳይያስ ጥናት አንጻር፥ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኘውን ክርስቲያን እንዴት ታጽናናዋለህ?

2. ሀ) ኢሳይያስ ሰዎችንና የእግዚአብሔርን ቃል ያነጻጸረው እንዴት ነበር? ለ) በንጽጽሩ ሊያስተምራቸው የፈለገው ምንድን ነው? ሐ) ደካሞች መሆናችንን ማስታወሱ ምን ያህል አስፈላጊ ነው?

3. ሀ) ኢሳይያስ በእግዚአብሔርና በጣዖታት መካከል የሚገኘውን ልዩነት ለአይሁዶች የገለጸው እንዴት ነበር? እግዚአብሔር ከጣዖታት እንደሚበልጥ ለማረጋገጥ የተጠቀመባቸው መረጃዎች ምንድን ናቸው? ለክርስቲያኖች ይህንን እውነት ማስታወሱ ለምን ይጠቅማል? ለ) ኢሳይያስ ለአይሁዶች እግዚአብሔር የዓለምን ታሪክና የነበሩበትን ሁኔታ እንደሚቆጣጠር ያሳያቸው እንዴት ነበር? ክርስቲያኖች

አስቸጋሪ የሕይወት ፈተና በሚጋረጥባቸው ወቅት ይህንን እውነት ማስታወሳቸው ለምን ይጠቅማል?

4. እግዚአብሔር ጠንካራ ብላቴኖች እንኳ በምድር ላይ ሕይወታቸው ሊደክሙ እንደሚችሉ ተናግሮአል። ሀ) እግዚአብሔር በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ለሕዝቡ እንደሚያደርግላቸው ቃል የገባው ነገር ምንድን ነው? ለ) ከንስር በረራ እንደሚታየው በችግሮችና በዕድገት መካከል ያለው ዝምድና ምንድን ነው? ሐ) እግዚአብሔር ቃል የገባውን ብርታት ለማግኘት ሰዎች ሊያደርጉት የሚገባው ነገር ምንድን ነው? መ) እግዚአብሔር በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በሕይወትህ ልዕለ-ተፈጥሮአዊ ኃይል የሰጠባቸውን ጊዜያት ለሌሎች አካፍል።

5. ሀ) የእግዚአብሔር ባሪያ የሆነችውን እስራኤልን፥ የእግዚአብሔር ባሪያ ከሆነው ከመሢሑ ጋር አነጻጽር። ለ) የእግዚአብሔር ፍጹም ባሪያ የሆነው የመሢሑ ባሕርያትና ተግባር ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሞዴል የሆነው እንዴት ነው? ሐ) ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይህንኑ ሞዴል መከተል ከባድ የሚሆነው ለምንድን ነው? የመሢሑ ባሕርይ ካላቸው እንዴት ሊለወጡ ይችላሉ? መ) በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከመሢሑ ባሕርያት ለመከተል ከሁሉም በላይ የሚከብደው የትኛው ነው? ለምን?

6. ሀ) ከእነዚህ የትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፎች ስለ መጨረሻው ዘመን ምን እንማራለን? ለ) ምእመናን እግዚአብሔር እንደሚፈልጋቸው ለመኖር ሊከተሉዋቸው የሚገቧቸውን እውነቶች ዘርዝር። ሐ) ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ ባሕርዩና በዓለም ውስጥ ስለሚያካሂዳቸው ተግባራት የተማርሃቸውን ነገሮች ዘርዝር።